# በበጌምድር እና ስሜን ጠቅላይ ግዛት[1] የተነገሩ ምጸትለበስ የቃል ግጥሞች ከታሪክ ዕይታ አንጻር[2]

**ኢብራሒም ዳምጠው[3]**

**አጠቃሎ**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ምጸትለበስ የቃል ግጥሞችን በመተንተን የቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ መንግሥትን የላዕላይ አስተዳደርና የሕዝቡን ፖለቲካዊ ዕይታ ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡ የቃል ግጥሞቹ በተለያዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች የተሰበሰቡ ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል ኢመደበኛ ቃለመጠይቅ እና ጥልቅ ውይይቶች ይጠቀሳሉ፡፡  በጥናቱ ቀደም ሲል የተሠሩ የምርምር ሥራዎችንም የመዳሰስ ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣ ገላጭ  ዘዴን በዋናነት በመጠቀም  መረጃዎችን ለመተንተን ጥረት ተደርጓል፡፡ ጥናቱ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን የሥልጣን ዘመን፣ በተለይም ኢትዮጵያ ከጣሊያን ወረራ ነጻነቷን ካገኘችበት ከ1933 እስከ 1966 ዓ.ም. አብዮት ፍንዳታ ድረስ ያለውን ዘመን የሚመረምር ሲሆን፣ የተጠቀሰው ዘመን ፖለቲካዊ ጉዳዮች ከሞላ ጎደል በተመረጡት የቃል ግጥሞች አስረጂነት ተዳስሰዋል፡፡ የቃል ግጥሞቹ በአብዛኛው በአፄ ኃይለሥላሴ የቤጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎች የአስተዳደር ዘይቤዎች ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በጥናቱ የሕዝቡን ጥልቅ የፈጠራ ዐቅም፣ የፖሊቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ትንታኔ ዕውቀቱን፣ ክህሎቱን፣ እንዲሁም ሐሳቡን የመግለጫ ስልቱንና ዐቅሙን ለማየት ተሞክሯል፡፡ በዚህም የቃል ግጥሞቹ የኅብረተሰቡን ጥበብና የመግለጽ ዐቅም የሚያሳዩ፣ ኅብረተሰቡ ያሞገሰና ያመሰገነ በሚመስል ወይም በቀልድ መልክ የፖለቲካ ብሶቱን እርስ በርሱ የሚለዋወጥባቸው እና ለሚመለከተው የኅብረተሰብ ክፍልም ለማስረዳት የሚጠቀምባቸው ቅርሶች እንደሆኑ ከጥናቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ባጠቃላይ ጥናቱ ፖለቲካዊ ጭብጥ ያላቸውን ምጸታዊ የቃል ግጥሞች መሠረት አድርጎ ትንተና የሰጠ ሲሆን፣ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ  ዘመነ መንግሥትን የሕዝብ አስተዳደር፣ እንዲሁም የተራው ሕዝብ እና የላዕላይ መዋቀሩ ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበር አሳይቷል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፤ ምጸት፣ ቃል ግጥም፣ ፖለቲካዊ፣ በጌምድርና ስሜን፣ ኢትዮጵያ**

[1] ይህ ጥናት በቀድሞ በጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት አካል፤ በአሁኑ የሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን አካባቢ የተሰበሰቡትን የቃል ግጥሞች ይተነትናል፡፡

[2] ሥነቃል በባሕሪው በጊዜ ሊገደብ ስለማይችል ጥናቱ የግርማዊ ቀዳማዊ ንገሠ ነገሥት ኃይለሥላሴን ዘመን በተለይ ከጠላት ወረራ በኋላ እስከ አብዮቱ ያለውን ጊዜ ይዳስሳል (1933-1966 ዓ.ም.)

[3] በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተባባሪ ፕሮፌሰር

## 1. የጥናቱ ዳራ

የጥናቱ አካባቢ የሀገሪቱን ሁሉንም የአየር ንብረት ዓይነቶች የያዘ ሲሆን፣ የሕዝቡ የአኗኗር ዘይቤም በግብርና፣ በዕደጥበብና በንግድ ሥራዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የአካባቢው ሕዝብ ታሪኩን፣ ወጉንና ልምዱን፣ እንዲሁም የዕለት ከዕለት ኑሮውን፣ ባህሉን በቃል ግጥም አማካይነት በሰምና ወርቅ የመግለጽ ረጅም ታሪክ አለው፡፡[4] የቃል ግጥም በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሊከወን ይችላል፡፡ በተለይም አዝማሪዎች፣ እረኞች፣ ሙሾ አውራጆች፣ እንዲሁም ሀሚናዎች በይበልጥ የቃል ግጥምን የሚጠቀሙና በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ቢሆንም፣ ሌላው የማኅበረሰብ ክፍልም[5] በቃል ግጥም ስሜቱን ይገልጻል[6]፡፡

የቃል ግጥም በዓይነቱና ቅርጹ በርካታ መልኮች ያሉት ሲሆን፣ ይህ ጥናት ምጸትለበስ በሆኑት ቃል ግጥሞች ትንተና ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡ የጥናቱ አካባቢ ካለው የከበረ የሥነቃል ሀብት ክምችት አንጻር "አባይን በጭልፋ" ያክል እንጂ ብዙ መዳሰስ ያለባቸው ጉዳዮች በጥናቱ አልተዳሰሱም፡፡ ያም ሆነ ይህ ለዘርፉ ጥናት ተነሳሽነት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡[7]

---

[4]Ebrahim Damtew,"History through oral poetry: Peasant Responses to Land Reform and Land Redistribution in Gondar province, 1975-1982", *Northeast African Studies* ,Vl.18, Nos.1-2 (2018), pp.95-97; Donald Crummey, "Literacy in an Oral Society: The Case of Ethiopian Land Records, *Journal of African Cultural Studies*18, no.1, Language ,Power and Society: Orality and Literacy in the Horn of Africa, (Taylor & Francis, 2006), pp.9–22; አለቃ ይኩኖአምላክ ገብረሥላሴ፣ "የቀድሞ ቅኔዎች ከነትርጓሜያቸው"፣ *የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መጽሔት* Vol. IV,No.1(1966)፣ገጽ፣ 76-77፤ አርኖ ሚሸል ዳባዲ ተረጓሚ ገነት አየለ፣ *በኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች ቆይታዬ*፣ (2009 ዓ.ም)፣ገጽ 78-9፤አዲስ ዘመን ጋዜጣ ነሐሴ 9/1972፣ ገጽ፣ 8-9 "የጎንደር ሕዝብ የቅኔና የኪነት ሰው" ስለመሆኑ ማስገንዘቢያ በአቶ አውላቸው ደጀኔ በወቅቱ የጎንደር ሀገረሰብ ሙዚቃ አሠልጣኝ ተብራርቷል፡፡

[5]የኔታ ተሾመ አደፍርስ ዕድሜ 85 ዓመት፣ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ፣ ጎንደር ከተማ፤11-14/4/ 2005 ዓ..ም እና 4/5/2006 ዓ.ም.

[6]Ebrahim, 2013, pp,1-5፣ፈ.ቃደ፣1991 ገጽ፤84፡፡

[7]በ2006ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል ሀምሳኛ ዓመቱን "Historiography and a Half-century of Radicalism in Ethiopia" በሚል ርእስ ዓለም አቀፍ ዓውደ ጥናት ባዘጋጅበት ወቅት ወረቀቱን አቅርቤ ያገኘኋቸው ገንቢ ሳይንሳዊ አስተያየቶች እንደመልካም አጋጣሚ የሚወሰዱ ናቸው፡፡ ፕ/ር ሹመት ሲሻኝ ፣አቶ ደባሽ ይማም ፣አቶ አውግቸው አማረና አቶ ጋሻው አሻግሬ ይዘቱን በመገምገም፤ ዶ/ር ኤፍሬም ጥሩነህ በተለይ በአርትኦት ሥራው ስላገዛችሁኝ፣ ስላበረታታችሁኝና ሙያዊ ግዴታችሁንም ስለተወጣችሁ ፈጣሪ አምላክ ያክብርልኝ፡፡ እማላውቃቸው ሁለት የዘርፉ ባለሙያዎች ወረቀቱን ገምግማችሁ እኔ ያላየሁትን በማየት ስላስተማራችሁኝና ገንቢ አስተያየት በመስጠት ሥራው የተሻለ እንዲሆን ስላደረጋችሁ እናንተንም ሙራዳችሁን አምላክ ይሙላልኝ፡፡ በመጨረሻም የኢትዮጵያ ጥናት መጽሔት አርትኦት ሥራ አስኪያጅ ዶ/ር ብርሃኑ አስፋው

## 2. የጥናቱ ዓላማ

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ከ1930ዎቹ እስከ 1960ዎቹ አጋማሽ ድረስ የበጌምድር እና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ሕዝብ በዘመኑ የቃኛቸውን ፖለቲካዊ ዕይታዎች በምጸትለበስ የቃል ግጥሞች አማካይነት በመዳሰስ ከታሪክ አንጻር ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡

## 3. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በገላጭ የምርምር ንድፍ የተከወነ ሲሆን፣ መረጃዎቹም ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተሰብስበዋል፡፡ ከአዝማሪዎች፣ ከሙሾ አውራጆች፣ ከቤት እመቤቶች፣ ከገበሬዎችና የአካባቢውን ታሪክ ከሚያውቁ የዕድሜ ባለጸጋ አባቶችና እናቶች ጋር ቃለምልልስና ውይይት ተደርጓል፡፡ የቃል ግጥሞቹ ባብዛኛው በቀጥታ የሚሰበሰቡ ባለመሆናቸው በተደጋጋሚ ልዩ ልዩ ዐውዶች ላይ ለመገኘት ጥረት ተደረጓል፡፡ ለምሳሌ፤ ድግስ ቤት፣ ለቅሶ ቤት፣ ሰርግ ቤት፣ እንዲሁም መሸታ ቤት በመገኘትና በመሳሰሉት መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡ አንዳንድ ጊዜም በጉዞ ላይ ከሰዎች ጋር በተደረጉ ውይይቶች በእግረመንገድ የተሰበሰቡ መረጃዎችም አሉ፡፡ ቃል ግጥሞቹ ባብዛኛው ባልተጠበቁበት ቦታ ከመገኘታቸው አንጻር ተገጠሙ ከተባለበት ቦታ ብቻ ሳይሆን ከሌላ ቦታም ሊገኙ ስለሚችሉ ይህን የሥነቃል ባሕርይ ከግምት ውስጥ ለማስገባት ጥረት ተደርጓል፡፡ በጥናቱ በዋነኛነት የተሳተፉት አዝማሪዎች፣ ሙሾ ደርዳሪዎች፣ በሽለላና ፉከራ ሙያ የታወቁ ሰዎች ሲሆኑ፣ አመራረጣቸውም ለቡድን ተኮር ጅምላ ውይይት እና ለቃለመጠይቅ የመጀመሪያ ሙከራ ከተመረጡት ሰዎች መካከል በማብራራት ብቃትና በግንዛቤ ብስለት የተሻሉት በቁልፍ መረጃ ሰጪነት ተመርጠዋል፡፡ በተጨማሪም ጠቋሚ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴን (ስኖው ቦል) በመጠቀም የጥናቱን ዓላማ መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ወደ ተመረጡ መረጃ ሰጪዎች በመሄድ መረጃውን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በጥንቃቄ የተመረጡት መረጃ ሰጪዎች የምጸትለበስ ግጥሞቹን ግልጽ በማድረግ ረገድ ድርሻቸው የጎላ ነበር፡፡ በተሰበሰቡት ግጥሞች ላይም ከተመረጡት ሰዎች ጋር ጥልቅ ውይይት ተደርጓል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱም መዛግብትን ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡ መዛግብቱ ከቀድሞ የጎንደር ክፍለ ሀገር አስተዳደር ሕንጻ ክፍል የተገኙ ናቸው፡፡ ከርእሱ ጋር ሊዛመዱ ይችላሉ ተብለው የተለዩ ዋቢ መጻሕፍትን ጭምር በጥናቱ ለማካተት ጥረት ተደርጓል፡፡ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡትን መረጃዎች በተገቢው መንገድ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ባጠቃላይ 56 የቃል ግጥሞች የተሰበሰቡ ሲሆን፣ 25 ያክሉ ለትንተና ተመርጠዋል፡፡ አንዳንዶቹም በግርጌ ማስታወሻ ጭምር በአጋዥ ማብራሪያነት ተካተዋል፡፡ በመጨረሻም

ጊዜ በመውሰድ በጥልቀት በመገምገም ለሰጡኝ ገንቢ አስተያየት ምስጋናዬ በፈጣሪ ሥም የላቀ ነው፡፡

ለትንተና ያመች ዘንድ ግጥሞቹ በጭብጥ በጭብጥ ተከፋፍለው በገላጭ የትንተና ስልት በሐተታ ቀርበዋል፡፡ ጭብጦቹም ሁለት ሲሆኑ፣ ሀገራዊ ዘውግ ያላቸው የቃል ግጥሞችና አካባቢያዊ ዘውግ ያላቸው የቃል ግጥሞች ተብለው ተሠይመዋል፡፡

## 4. የቃል ግጥም አከዋወን

ቃል ግጥም ትርጉም ባለው መልኩ ለተደራሲ አንድን ቁምነገር ጠቅለል አድርጎ ለማስረዳት የሚችል የፈጠራ ውጤት ነው፡፡ እዚህ ላይ ክዋኔ ማለት አንድን ረቂቅ ነገር ነብስ ዘርቶ ለተደራሲው ግልጽ አድርጎ ማሳየት ማለት ሲሆን፣ ክዋኔው የእያንዳንዱ ተደራሲ ሕይወት አካል ሊሆን ይችላል፤ ስሜቱንም ሊያይበት ይገባል የሚሉ ምሁራዊ ትንታኔዎች አሉ፡፡[8] ከዋኙም የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ በማብላላት ነብስ ዘርቶበት ትርጉም እንዲኖረው ያደርገዋል[9]፡፡ ክዋኔ ቃል ግጥሙን በመጠቀም በዘፈን፣ በለቅሶ፣ በፉከራ፣ በሽለላ፣ በእንጉርጉሮና በመሳሰሉት የሚቀርብ ነው፡፡[10]

## 5. በጥናቱ የተካተቱ የቃል ግጥሞች ይዘት ቅኝት

ሥነቃል በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ እንደ አንድ የዕወቀት ምንጭ የሚጠቀስ ቅርስ ነው፡፡ የሀገረሰብ እንጉርጉሮዎች፣ ቀረርቶዎች፣ ዘፈኖችና ግጥሞች ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ለሕዝቡ የማንነት መስታወትና የዕለትተዕለት ኑሮ መገለጫነታቸው የጎላ ነው፡፡ ከዚህ ጋር የሚነሡት አዝማሪዎች፣ ሙሾ አውራጆች፣ ሀሚናዎች/ አባውዴዎች/ እንዲሁም እረኞች ከጥንት ጀምሮ የሙያው ባለቤቶች ናቸው፡፡[11] ይህ ሲባል አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ተሳትፎው አናሳ ነው ለማለት እንዳልሆነ ልብ ይሏል፡፡ ምን ተይዞ ጉዞ እንዲሉ እንዲያውም ለእኚህ የጥበብ ሰዎች ትምህርት ቤታቸው፣ ቃል አቀባያቸውና አስተማሪያቸው፣ ስለችሎታቸው ማስመስከሪያ፣ ለሙያቸው ዕውቅና

---

[8]RuthFinnegan, *Oral Poetry*, London: Cambridge University Press, 1977), p.16፤ ፈቃደአዘዘ፣ *የስነቃልመመሪያ*፣አዲስአበባ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣(1991)፣ገጽ: 84-88፡፡

[9]*ይመር እምሩ* (አዝማሪ) *ዕድሜ* 76፣*ቃለመጠይቅ የሰጡበት ቦታ*፣ ቡርባክስ፤ *ቀን* 5-9/3/ 2006 *ዓ.ም*.

[10]*ፈቃደ አዘዘ*፣ “ቁዘማ፤ (ፎክሎር )”*ባህልና ልማት በኢትዮጵያ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች አርታኢ ሽፈራው በቀለ*፤ አሳታሚ ፎረም ፎር ሶሻል ስቴዲስ፤ አዲስአበባ፣ 2004 ገጽ፤97-132)፤ዘሪሁን አስፋው 2002፡፡ *የስነጽሑፍ መሰረታዊያን*፡ *አሳታሚ*፡፡ *ንግድ ማተሚያ ድርጅት*፣*ገጽ*፣20-27፡፡

[11]Misganaw Andualem,“Change and continuity in the lives of BurbuaxAzmaris in Gondar Zuria Woreda”, (MA Thesis in the Department of Social Anthropology, A.A.U፣,2011),pp.5-28; Ebrahim Damtew, “Observing Ethiopian Minstrels: an Indigenous Musicians and Singers (*Azmari)* in North Gondar zone” *The Asian Man - An International Journal.*Volume 7,(2013), p.97.

የሚሰጣቸው በተለምዶ "አልተማረም" የሚባለው ሰፊው ሕዝብ ነው። ባብዛኛው በክወናው ቅድሚያ የሚሰጠው ግን ለተጠቀሱት የኅብረተሰብ ክፍሎች መሆኑ አያጠያይቅም። ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀደም ባሉት ዘመናት ማኅበረሰቡ ጉዳዮቹ እንዲነገሩለት የሚፈልገው በአዝማሪዎች፣ በሙሾ አውራጆች፣ እንዲሁም በእረኞች በኩል ነበር።[12] ሕዝብና መንግሥትን በማገናኘት እንደ ድልድይ ሲቆጠሩም ነበር። ለዚያም ይመስላል በቀድሞው ጊዜ “አዝማሪ ምን አለ? እረኛ ምን አለ?” ወይም “ምን ተብሎ ተለቀሰ?” ተብሎ የሚጠየቀው። ከዚሁ ጋር ተያይዞም ብዙ ነገሥታት ቆም ብለው የሕዝቡን ድምፅ በማዳመጥ መንግሥታቸውንም ሆነ ሕዝቡን ተጠቃሚ ያደርጉ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ።[13] ለዚህም ይመስላል በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመንና ከዚያም በፊት የጥበብ ባለሚሎች በተለይ አዝማሪዎች እየተመለመሉ በሥነግጥም አከዋወናቸው በምጸት፣ እንዲሁም በሰምና ወርቅ ንግግራቸው የቤተመንግሥት ባለሟል የሚሆኑት። የጠቅላይ ግዛት ሊቀመኳስ /አዝማሪ/ በተዋረድ ላሉት አስተዳደራዊ ሰንሰለቶች የመሳፍንት አጫዋቾች አዛዥ ተደርገውም የሚወሰዱበት ሁኔታ ነበር።[14] በአብዛኛው ሥራቸውም የማኅበረሰቡን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር መተንተን ነው። ማዝናናትም ሌላው ተግባራቸው ነው፤ የተዋጣለት የዜና መዋዕል ሥራና ፍሰቱ ያማረ የታሪክ ዘገባ የሚሠሩም ነበሩ። እንደየሁኔታው የኅብረተሰቡን ጉዳዮች ለሚመለከተው አካል ወይም ለሕዝቡ በምጸትም ይሁን በቅኔ ያስረዳሉ። ስለዚህም ነው የጋዜጠኝነትና የመገናኛ ብዙሃን ሥራ ይሠሩ እንደነበር የቀድሞ የመንግሥት ባለሥልጣናት የሚያስረዱት።[15] በንጉሡ ዘመን ባከዋወናቸው ላቅ ያሉ ጥበበኞች /ሊቀመኳሶች/ ትልቅ ክብር ከሚሰጣቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ጎራ የሚሰለፉ እንደነበር እንረዳለን።[16] ሊቅ የሚባለው የክብር ስም የተሰጣቸው ከሞያቸውና ከአከዋወን ብቃታቸው፣ ሥርዓተመንግሥትን

[12]Feqade Azeze, *Ethiopia the Challenge of Democracy from below .Forum for Social studies* in Bahru Zewde and Pausewang,Siegfried (ed.)”Oral Literature Depicting the man, His Regime officials and proclamations”, (Addis Ababa*:Forum for Social Studies,Press*, 2006), p. 149.

[13] ፈቃደ፣2004፤ ገጽ፤97 ,Fekade Azeze , 2006,p. 14)

[14]በሁሉም፣ 2009 ዓ.ም.፣ ገጽ 93፤ Teclehaimanot G/sillassie, “Abrief ሽurvey for the Study of the Azmari in Addis Ababa” *In the proceeding of the international symposium for the centenary of Addis Ababa,* edited Ahmed Zekaria, Bahru Zewde and Taddese Beyene (A.A.U, IES,1986)፣pp,161-172.

[15] የቃል መረጃ ሰጪ፡- (*አጋፋሪ*) አበበ አየለ ዕድሜ 85 ዓመት፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ ጎንደር፣ 3/2/2005 እና 2/2/2005 ዓ.ም. ሲሆኑ፣ በንጉሡ ዘመን በቤተመንግሥት አሳላፊነት የሠሩና የቤጌምድር እና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ታሪክን ጠንቅቀው የሚያውቁ ናቸው።

[16]*ዝኒከማሁ፤አዝማሪ* በሬ ፋሌ ዕድሜ 71፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ ጎንደር፤ 3/3/2005 እና 2/2/2006 ዓ.ም.

በሚገባ ማወቃቸውና መተንተን በመቻላቸው የተነሣ እንደሆነም ይነገራል። ይህ የጥበብ ትምህርታቸው በተለምዶ በትውልድ ይገኝ የነበረውን የቤተመንግሥት ባለሚልነትን እንዲያገኙ አድርጓቸዋል።[17]

በቀድሞው በጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ከሊቀመኳስነት ባሻገር የዘመኑ ከፍተኛ "የሹመት" እና የክብር ስም ይሰጣቸው እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። የቀኝአዝማችነት፣ የግራአዝማችነት፣ የባላምባራስነትና ፊታውራሪነት የማዕረግ ስሞችን መጥቀስ ይቻላል። እንደ አንድ የአውራጃ ገዥ ባለአምስት ወይም ባለስድስት ጠመንጃ ያዥ ወታደሮች ያጅቧቸው እንደነበርና ባለርስትም እንደነበሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ።[18.]

ወደ ክዋኔ ግብር ስንሄድም ንጉሡና አቡኑ ቢኖሩም እንኳ ሊቀመኳሱ በሌሉበት ሥርዓቱ አይጀመርም። ማንኛውም ሀገርን፣ ሕዝብንና መንግሥትን የሚፈታተን የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ በተከሰተ ጊዜ ሕዝቡን ንቃ የሚሉት በተለይ አዝማሪዎች ናቸው። አዝማሪዎች እነዚህን ሁሉ ሥራዎች በቃል ግጥምና በዜማ በማሳመር በሳልና ስሜት ቀስቃሽ ባህልና ታሪክ ቀመስ አባባሎቻቸውን ከትውልድ ትውልድ ሲያስተላልፉ ቆይተዋል። የማኅበረሰቡን የለውጥ ጥያቄም እንዲሁ ግንባር ቀደም በመሆንና ቃላዊ ክዋኔ በመስጠት ይታወቃሉ። ከዚህም በመነሣት ነው በአዝማሪ የሚነገሩ የቀድሞ የቃል ግጥሞች ብስለት ያላቸው ናቸው የሚባለው።[19] አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በአንድ ትከሻ ጠመንጃ በሌላኛው መሰንቆ ይዘው ሲታገሉ ኖረዋል።[20] ለምሳሌ፤ በአምስቱ ዓመት የጣሊያን ወረራ ጊዜ ተብሎ የሚታወቀውን ማለትም፤ (ከ1928-1933 ዓ.ም.) ከጣሊያን ጋር በነበረው ያንገዛም ባይነት መራር ትግል ወቅት አዝማሪዎች

---

[17](ኢጋፋሪ) አበበ፣ (አቶ) ሽመል ደምለው፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ ጎንደር፣ 3/1/2004፣ 5/4/2005 እና 2/2/2006 ዓ. ም.፣ ወርቁ ገሠሠ፤ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ ጎንደር፣ 3/3/2005 እና 2/2/2006 ዓ.ም.፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ ጎንደር፣ 3/4/2004 እና 2/2/2005 ዓ.ም.፣ በሬ፤ በሁሉም፣2009፣ገጽ፣93-4)

[18]*ዝኒከማሁ*፣ ኢጋፋሪ አበበ አየለ፣ (አዝማሪ) ሲሳይ ቦጋለ ዕድሜ፣ 78 ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ፣ ቡርቧክስ፤ 13/1/2005 እና 10/13/2006ዓ.ም.፣ ዋኘው ለገሰ ዕድሜ፣ 83 ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ፣ ጎንደር፤ ቀን 1-3 /1/ 2006ዓ.ም።

[19]ደበበ ሰይፉ፣ "ያማርኛ ሕዝባዊ ስነግጥም ለአብነት ያህል"፣ *የቋንቋ ጥናት ኢንስቲዮት መጽሔት*፣ቅጽ 1.ቁ.1፣ (ኢ.ኢ.ዩ፣1983) ገጽ፣31፤ ጌቴ ገላዬ ፣"ከ1983 *የመንግሥት ለውጥ በኋላ የምሥራቅ ጎጃም ገበሬዎች ፓለቲካዊ ግጥሞች*"፣*Proceeding of the XIV International Conference of Ethiopian Studies*, Volume,3, (2000),pp. 1045-46;Ebrahim Damtew ,"The shifting status of the Gondar Azmari in Revolutionary Ethiopia : from out cast to popular stars", *Ethiopian Renaissance Journal of Social Science and Humanities* 4,1,(2017),pp.45-46; Getie Gelaye, "Peasant Poetics and State Discourse in Ethiopia: Amharic Oral Poetry as a Response to the 1996–1997 Land Redistribution Policy," *Northeast African Studies* 6, nos.1–2, New Series (1999), pp.171–206.

[20](አቶ)አስቻለው በለጠ፣ ዕድሜ፣ 82 ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ ማክሰኝት፤ 3/4/2005 እና 2/1/2006 ዓ..ም.፤ ገሪማ ታፈረ፣ *ጎንደሬ መጋሻው* ፤(አዲስ አባባ 1949) ገጽ፣ 241።

የነበራቸውን ብርቱ የሀገር ፍቅርና የመምራት ብቃት ብዙዎች ያስታውሱታል፡፡ ለምሳሌ፤ ቀኛዝማች ምስጋናው አዱኛ፣ ሊቀመኳስ ታዬ በድሉ፣ ሊቀመኳስ አንዳርጌ ጉልችን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡[21]

## 6. ምጸታዊ የቃል ግጥም

የዘርፉ ምሁራን ምጸታዊ ንግግር ወይም ቃል የሚያተላለፍበት መንገድ እንደየተጨባጭ ሁኔታውና እንደተደራሲያኑ አረዳድ የሚቀያየር መሆኑን አበክረው ይናገራሉ፡፡[22] ምጸትን መቼ እጠቀማለን? የምጸት ዓላማስ ምንድን ነው? እና ሌሎችንም መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ የሚከተሉትን ትንታኔዎች ምሁራኑ አስቀምጠዋል፡፡ ምጸት እውነታውንና በተግባር እየታየ ያለውን ጉዳይ በድብቅ ለማኅበረሰቡ ለማሳወቅ ይጠቅማል፤ ተግባሩም በቀልድ፣ ያልታሰቡና ግልጽ የማይመስሉ (comic) አርት (ጥበብ) በመጠቀም ግለሰቦችን፣ መንግሥትን ወይም ማኅበረሰቡን መተቸትን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህም ግነት (ጉዳዩን በማግዘፍ) እና በቀልድ መልክ ለሚመለከተው አካል ያደርሳል፡፡ ሽሙጥ (ምጸት) የለውጥ ጥያቄን በቀጥታ ከመጠቆም ይልቅ በሌላ መልክ አስመስሎ ማስረዳት የሚችል በቀላሉ ሊገባ (ግልጽ) ሊሆን የማይችል ነገርን ቀለል አድርጎ ያየ በሚመስል መልክ ብዙ ብሶትና ችግርን ያዘለ ጥበብ ነው፡፡ ምጸት ደስታንና ፈገግታን እየሰጠ የያዘውን ብርቱ ጉዳይ ሊገልጽ የሚችል መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤትም እርማት ወይም መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ፍለጋ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡[23]

ባጠቃላይ ምጸት የኅብረተሰቡንና የግለሰቦችን ዕለታዊ ሁኔታዎች ሊዳስስ የሚችል የጥበብ ሥራ ሲሆን፣ በግነት፣ በገሎ ማዳን፣ በሽሙጥና በማዝናናት እያስመሰለ ውስጠወይራ በሆኑ ቃላት በመታገዝ ለለውጥ መሳሪያነት የሚሠራ ነው፡፡ ወይንም ምጸት በሳቅ ሐዘንን፣ በደስታ መከፋትን፣ በምክር ስድብን፣ በከበሬታ ውርደትን፣ በድል ሽንፈትን በጎንዮሽና በተቃርኖ አነጋገር የሚገልጽ ነው፡፡ ከላይ ለማብራራት እንደተሞከረው ምጸት አሠራሮችን በማጋለጥ ለለውጥና ለተሻለ ሕይወት የሚያታግል ጥበብ ነው፡፡

የምጸት ዋና ተግባር ለውጥ ማምጣት፣ አደገኛ ችግር የሚፈጥሩ ፍትሐዊነት የጎደላቸው አሠራሮች ላይ እርምት መስጠትና ሌሎች ሰዎችም መልካም ሥራ እንዲሠሩ ማስተማር ነው፡፡[24] ምጸት ለፍትሕ፣ ለሞራልና

---

[21] *ዝኒከማሁ፡፡*

[22]Sentayehu Genet, "Political and Social Satire in Bewketu Siyoum's Enqilf ena Edimie and Berari Kiteloch'',( M.A Thesis in Foreign language and Literature, A.A.U. 2008),pp.24-30.

[23] (Frienberg, 1967,pp18-56, pp,1-23፣ዘሪሁን ፤2002፣ገጽ፤125).

[24](ዘሪሁን ፤2002፣ገጽ፤125-126፣Harris,R, *The Purpose and Method of Satire*: www.virtual salt. Com satire Atm (2008),pp.236- 8

ለሥነምግባር ተገዥነት ከፍተኛ አስተምህሮ ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ የምጸት አገላለጽ ዓላማ ሰዎች የተውትን በጎ ነገር፣ መተሳሰብና መከባበር ይዘው ይቀጥሉ ዘንድ ማበረታታት ነው፡፡[25]

ከዚህ በታች የሚተነተኑት የቃል ግጥሞች ምጸትለበስ ሥነቃል በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ የሚያሳዩ ናቸው ብሎ ደራሲው ያምናል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሰው ዘመን በዋናነት ፖለተካዊ ጉዳዮችን የሚያነሡ ምጸትለበስ ቃልግጥሞች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

## 7. ፖለቲካዊ ጉዳዮችን መሠረት ያደረጉ ምጸታዊ የቃል ግጥሞች

ቃል ግጥሞቹ ባብዛኛው ፖለቲካዊ ይዘት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ሲሆን፣ ይዘታቸውም ሀገራዊና ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይህም የሆነበት በዋናነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ውስንነትና ትኩረታቸው በተጠቀሰው ይዘት ላይ በመሆኑ ነው፡፡

### 7.1 ሀገራዊ ጭብጥ ያላቸው የቃል ግጥሞች

በአንድ አካባቢ የሚነገሩ የትችት ግጥሞች የአካባቢውን መሪዎችና ኅብረተሰብን ብቻ የሚያዩ ሳይሆን የሀገር መሪዎችንና ሀገርንም እንደሚጨምሩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡[26] ከዚህ በታች የምናያቸው ግጥሞችም ከዚሁ የሚመደቡ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡

1) አባ ጠቅል ኃይሌ ስንት ነው ሱሪህ፣
የኢትዮጵያን ችግር ጠንቅቀህ ያየህ፡፡[27]

"ሱሪ" እንደ ሀገሬው ባህል ትልቅ ትርጉም ያለው ነው፡፡ ባብዛኛው ከድል ማድረግ ጋር የሚያያዝ የጀግንነት ምልክትም ነው፡፡ ሌላው በተቃራኒው ሽንፈት ጋርም ሊያያዝ ይችላል፡፡ "ሱሪውን ፈታ" ከተባለ ሽንፈትን ውርደትን ያመለክታል፡፡ ሱሪ "ታጠቀ" ወይም "ሱሪ አሥታጠቀ" ከተባለ ጀብድ ለሀገር ለወገን ክብር የሚሆን ሥራ መሥራትን ይወክላል፡፡

[25] Feinberg,1963,p,71;ዘሪሁን፤2002፣ገጽ፤125-126.
[26] (ፈቃደ ፤2006፣ገጽ፤168፤ Feqade ,1998, pp.3-221.
[27] ወርቁ ገሠሠ፤ በተጨማሪ

"የይሁዳ አንበሳ ታላቅነው ሐይልህ ፣

ለኢትዮጵያ መድኃኒት ተወልደህ መጣህ"፡፡

"የተፈተነ ነው ካብረሃም ከሙሴ፣

መድኃኒትነቱ የኃይለሥላሴ"፡፡ እየተባለ ተገጥሟል፡፡

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ከመሆናቸው አንጻር በዘመናቸው በርካታ በሁሉም ዘርፎች ለምሳሌ፤ በፖለቲካውም ሆነ በማኅበራዊ ዘርፍ በርካታ ሀገራዊ መልካም ሥራዎችን ቢሠሩም መሠረታዊ የማኅበረሰቡ ችግሮችን ለመፍታት ያልቻሉባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸውን ስንኞቹ ለመጠቆም ይሞክራሉ፡፡ ተያይዞም የሕዝቡ ዘርፈ ብዙ ችግሮች እየተባባሱ በመምጣታቸው በሥርዓታቸው ላይ የሕዝብ ጥያቄ እንዲነሣ አድርጎታል፡፡ ለምሳሌ፤ በግጥም 1 ላይ እንደተመለከተው "አባ ጠቅል" የሚለው ቃል የንጉሡን ፈረስ ስም የሚወክል ነው፡፡ በጎ ተስፋም ያዘለነው፤ ዳር ድንበሯ የታፈረና የተከበረ ነጻነቷ የተጠበቀ ሀገር የሚያስተዳደር መሪ የሚልም እንድምታም አለው፡፡ የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ታሪክ ሲዳሰስ ታዋቂ ሰዎችም ሆኑ ሌሎች በተዋረድ በፈረሶቻቸው ስም ይጠሩ ነበር፡፡[28] ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ባብዛኛው የሚታወቁት "በጠቅል" ነው፡፡ በጉዳዩ ዙሪያ ያነጋገርኳቸው የዕድሜ ባለጸጎችና የታሪክ ዐዋቂዎች እንደሚያስረዱት፣ በዚህ የቃል ግጥም ተናጋሪው ንጉሡን በበጎ ዐይን ያየ በማስመሰል፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጉስቁልና ለመግለጽ እንደሞከረ ያስረዳሉ፡፡ የንጉሡ ዘመን የባላባቱና የመኳንንቱ ዕርስበርስ ሽኩቻ የበዛበት፣ ለግል ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ክብር የቆመና ብዙሃኑ የበይ ተመልካች የነበረበት ዘመን መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ምንም እንኳን በጥናቱ የተጠቀሰው ዘመን "ዘመናዊነት የተስፋፋበት" እየተባለ ቢጠራም በሁለቱም ማለትም፤ ሀገር ውስጥ ዕውቀትንና የውጩን ነባራዊ ሁኔታ አጣጥመው በመራመዳቸው የተመሰገኑ የሚባሉትን ወገኖች ጭምር ያላስደሰተና ሀገሪቱ የወደፊት ተስፋ የሚያጨልምና የሚጠበቀውን ያክል ለውጥ አላመጣም፡፡ ንጉሡም አንዳንድ ቀደምት ምሁራን ሀገራቸው መሆን ያለባትን በተለይ በፖሊቲካዊ፣ በማኅበራዊና በምጣኔ ሀብት አስተዳደር ዘመኑ የሚጠይቀውን ማድረግ ካልተቻለና ራስን መቻል ካልተቻለ ነጻ መንግሥት መሆን ብቻውን የትም እንደማያደርስ አበክረው ሲመክሩ፣ ምክሩን በተወሰነ መልኩም ቢሆን በመረዳት ንጉሡ የለውጥ እርምጃዎችን ለመውስድ ጥረት ሲያደርጉ ተስተውለዋል፡፡ ለምሳሌ፤ በትምህርት ዘርፍ፡፡ ምንም እንኳን ከጅምሩ የትምህርት ሥርዓቱ የሀገሪቱን ባህል ታሪክ ያገናዘበ አይደለም ቢባልም፣ ያም ሆኖ የተፈለገው ወደፊት መስፈንጠር ይቅርና የነበረውንም

[28] የቀድሞዎቹ ኢትየጵያዊያን ነገሥታት በአክሱም፣ በላስታ፣ በሸዋ፣ እንዲሁም በጎንደር ማእከላቸውን ባደረጉበት በጥንቱና መካከለኛው ዘመን ስመ መንግሥታቸውን አንበሳ ሰገድ፣ አጥናፍ ሰገድ፣ አድማስ ሰገድ፣አፅላፍ ሰገድ እየተባሉ ይጠሩ ነበር፡፡ ከጎንደር ዘመን በኋላ ስመ መንግሥታቸው በነገሥታቱ ፈረሶች ስም ላይ "አባ" እየተጨመረበት መጠራት እንደ ጀመረ ይነገራል (ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ* (አዲስ አበባ፣ 2000)፣ ገጽ. 96-97፡፡

ዕውቀት ወደማጣት ደረሰን የሚሉ ምሁራን አሉ፡፡[29] የንጉሡ ሥርዓትም ይህን የሕዝብ ብሶት ለመፍታት የወሰደው መፍትሔ አለመኖሩን፣ ቢኖርም አጥጋቢ አለመሆኑን ጭምር ይተነትናል፡፡[30]

ሕዝቡ "እንደንጉሡ ያጎንብሱ" እያለ መሪውን የማክበር መልካም ባህል ቢኖረውም፣ ንጉሡን "ፀሐዩ መንግሥት" በወላጁ ወይም በሃይማኖቱ መማሉን እየተወ "ኃይለሥላሴ ይሙት" እስከ ማለት የደረሰ ቢመስልም፣ የተጠቀሰውን ችግር ለመፍታት ለውጥ ፈላጊውን ኅብረተሰብ ጀሮ ሰጥተው አዳምጠው አብሮ ለመሥራት ያደረጉት ጥረት አናሳ መሆኑን ማኅበረሰቡ በቃል አቀበዮቹ በኩል ጠንቅቀህ ያየህ ጃንሆይ ፍጹም ነዎ፤ በርስዎ ደስተኛ ነን እያለ ያሽሟጥጣል፡፡ ንጉሡ በራሳቸው መንገድም ቢሆን ለውጥን ቢፈልጉም እንኳን መሳፍንቱ ፈቃደኛ እንዳልነበሩና ለመግዛት እንጂ ሕዝብ ለማገልገል የተሾሙ የማይመስላቸው ተብትበው እንደያዟቸው ይገለጻል፡፡ በንጉሡ ዙሪያ የበዙት ግብዞቹና አስመሳዮች ንጉሡን ሕዝቡ እንደሚወዳቸውና ባስተዳደራቸውም ደስተኛ እንደሆነ፣ በጎደለ እየሞሉ ይነግሯቸው እንደነበረ የሚያስታውሱ በርካታ ቃል አቀባዮች አጋጥመውኛል፡፡[31] ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ስንኞች ከዚሁ የታሪክ ዐውድ ጋር መረዳት እንደሚቻል መታዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ ተመሳሳይ የትችት ግጥም ቀኛዝማች ምስጋናው አዱኛ የራስ ጉግሳ (አባ ደልድል)[32] ቤተመንግሥት አዝማሪና ባለሟል ንጉሠ ነገሥቱ የጣሊያንን ወረራ በመቃወም ድፕሎማሲያዊ ጥረት ለማድረግ ወደ አውሮፓ ተሰደው ለዘመኑ ኀያላን መንግሥታት ለማስረዳት ማቅናታቸው በአርበኛውና "በተራው"[33] የሀገሬው ሰው ዕውቅና አልተሰጠውም ነበር፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚከተለውን ግጥም ተቀኝተዋል፡፡

---

[29]ዓይናለም አሸብር፣ *ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ሥራዎች*፣ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣2007 ዓ.ም.)፣ ገጽ፣xii-xiii፡፡

[30]ከዚህ ትንታኔ ጋር የሚስማሙ ብዙ ታሪካዊ ምርምሮች በምሁራን ቀርበዋል ፣Bahru,2008,pp,96-115; Desalegn,2009,pp,27-65;Fasil,Fasil Kiros, *TheSubsistence Crisis in Africa፡ The case of Ethiopia*. Organization for Social Science (1993), pp.29-33). በተለይም ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ ከ1937/8 ዓ.ም ጀምሮ ይወጡ የነበሩ የግብር ስሪት ለውጦች እና አስተዳደራዊ ችግሮች የገበሬውን ሁለንተናዊ ችግር ያገናዘቡ ሳይሆኑ ማእከላዊ መንግሥትን ብቻ ከማጠናከር አንጻር የሚታዩ ነበሩ፤ (Bahru, 2001,p,15;Debash,2011,pp,4-125)፡፡

[31]አበበ ማለደ፣ (አስር አለቃ), ምህረቴ ውቤ ዕድሜ 81 ቃልመረጃ የሰጡበት ቦታ አይከል፤ 12/5/2004 እና 2006 ዓ.ም.፡፡

[32] የራስ ጉግሳ ወሌ ቡጡል የፈረስ ስም፡፡

[33] የአካባቢውን ማንኛውንም ሹመት የሌለውን የአካባቢው ሕዝብ ለመወከል በቃል አቀባዮቹ የተመረጠ ቃል ነው፡፡

2) *ያልተገራ ፈረስ "ጠቅል" እያላችሁ*
*ልጓሙን በጥሶ ሎንዶን ገባላችሁ።*[34]

ከላይ እንደተጠቀሰው ፈረስ በኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ እጅግ የተከበረ እንሰሳ ነው። ነገሥታት፣ መኳንንት፣ የጦርሜዳ ጀግኖች ፈረስን ከመጓጓዣነትም አልፎ የዝናና የክብር ስም ጭምር አድርገውት እንደነበር ታሪክ ያስረዳናል። በቀድሞው የጭዋ ልጅ[35] አስተዳደግ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለው እንደነበረ ይነገራል።[36] ፈረስ እንደጦር መሳሪያ ጭምር ሚቆጠር የጀግና ጓደኛ ነው። ጌታው ፈረሱን ከመውደዱ የተነሣ በግብር አዳራሽ "ቼ በለው!" ብሎ አዝማሪው ወይም አቅራሪው ሲጀምር፣ ፉከራ ሲነሣ ባባቱ ወይም በራሱ መጠራቱን እየተወ በፈረሱ ይጠራል። በፈረሱም እጅግ ይኮራል፤ ለጦር ሜዳ ውሎም ሲፎክር የዳማ ጌታ! የዳኘው ጌታ! የጉራች ጌታ! የፈንዞ ጌታ! የታጠቅ ጌታ! የጉሎ ጌታ! እየተባለ ይፎከራል። ምክንያቱም የጎበዝ ስሙና የጦር ሜዳ ጓዱ ፈረሱ ስለሆነ። "አባ" የተሰኘ ቅጥያም ተጨምሮበት አባ ደልድል! አባ ዳኘው! እየተባሉ ባለፈረሶቹ ይጠሩ ነበር። የፈረስ ስም "አባ" የምትል አንዲት ቃል እንደ ግርማ ሞገስ የተጨመረበት ባብዛኛው የጌታውን ባሕርይ፣ ምኞቱንና ትንቢትን ጭምር የያዘ ሰፊ ትርጉም ስለለው ነው።[37] ቅጽል ስሙ በፈረሱ ቢሆንም የባለቤቱን ሙያ የሚናገርና የሚያሞግስ ስለሆነ እንደተባለው ጌታውንም ያኮራል። ለፈረስ ስም የሚሰጡት ስሞች ወኔን ቀስቃሽ ኀይለ ቃል የያዙ ናቸው።

ይህንንም በማስመልከት በተራ ቁጥር 2 በተጠቀሰው ግጥም "አባ ጠቅል" ተብለው በፈረሳቸው ስም የሚጠሩት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ናቸው። ገጣሚው በተለይ ከማይጨው ጦርነት በኋላ ሀገሪቱን ለጣሊያን ትተው ወደ አውሮፓ በድፕሎማሲ ሰበብ መሄዳቸው በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ ያልታወቀ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደነውርና የኢትዮጵያንም ክብር የነካ ተግባር ነው ተብሎ ይወራ ስለነበር፣ ከላይ የተገለጸውን የፈረስ ስም ሞያ ያልተወጡና ለቦታው የሚመጥኑ እንዳልሆኑም ቃል አቀባዮች

---

[34]በለጠ አበበ ጎንደር

[35] በቀድሞ ጊዜ ጠረፍ ጠባቂ ወታደሮች ጪዋ የሚባል ስም ነበራቸው። ለተሻለ ማብራሪያ፣ Merid W Aregay, "Military elites in Medieval Ethiopia", *Journal of Ethiopian Studies* Vol.30,No.1,(1997),pp.31-73; Tsehai Berhane-Sellassie, *Ethiopian Warrior hood: Defence ,Land and Society 1800-1941*, (Suffolk,UK: JamesCureency, 2018),pp.1-309;Hiroki,Ishikawa, "Change in the military system during the Gondar Period 1632-1767: the influence on the decline of the Solomonic dynasty" *In: Annalesd' Ethiopie*. Volume 18,annèe ,(2002), pp.2015-229.

[36]ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደ መስቀል፣ *ቼ በለው*፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ (አዲስ አበባ፣1961 ዓ.ም)፣ገጽ፣ 5-11።

[37] ዚነከማሁ።

ያብራራሉ።[38] አስተሳሰብዎ አልበሰለም፤ ለጠላት ጥለውን ሄዱ፤ ለምን አብረውን አይሞቱም? ሀገር ያለ ዳኛ ከብት ያለ እረኛ እንዴት ይሆናል? ንጉሥ ካለ ሰላም ዳመና ሳለ ዝናም እንዲሉ ጭምር።[39] ልጓሙን በጥሶ ማለት በሀገር ሕግ ሳይገዙ ጥሎውን ጠፉ፤ ብስለት የለዎትም፤ ያባቶችዎን ልማድ አፍርሰዋል፤ ስለሆነም በቦታው መቀመጥ የለበዎትም የሚል መራራ ሐሳብና ተቃውሞ ያዘለ እንደሆነ በመረጃ ሰጪዎች ይብራራል።[40]

በተጨማሪም ይህን በቁጥር 2 የተጠቀሰውን ትችት ወደጎን የተውት በማስመሰል ቀኛዝማች ምስጋናው በቁጥር 3 የተመለከተውን ተቀኝተዋል። ሆኖም ግን የሁለቱም ቅኔዎች መልዕክት ተመሳሳይነት እንዳለው ቃል መረጃ ሰጪዎቹ ይተነትናሉ።

3) ያልተገራ ጠቅል አትበሉ እባካችሁ፤
በእርሱ ላይ ተገኘ አበሻነታችሁ[41]

በማለት ሐበሻነትንና ነጻነትን የማይለያዩ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች በማድረግ ንጉሡን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት ተምሳሌት እንደሆኑ በማስመሰል፤ በተቃራኒው በሀገሪቱ ታሪክ ያልተለመደ ሥራ እንደሠሩና ሕዝቡን በመምራትና ከጠላት ጋራ በመዋጋት ፈንታ ጥለውት ወደባሕር ማዶ (አውሮጳ) መሄዳቸው አግባብ አለመሆኑን ተችተዋል። ንጉሡም በዚህ የተነሣ የብዙ ሕዝብ መነጋገሪያ ሆነው ባጅተዋል። ሕዝቡም በንጉሡ ላይ የነበረውን እምነት እንዲያጣ ሆኗል። ንጉሡ አምስት ዓመት እንግሊዝ ሀገር ቆይተው ጣሊያን ድል ሆኖ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ዙፋናቸውን ከያዙ በኂላ ወደ ጎንደር መጥተው "አንተ ተሳዳቢው አይደለህ? ላንምርህ በስቅላት ቀጥተንሃል።" ቢሏቸው፣ "ጃንሆይ! እንኳን በእኔ በደጉ ጌታዬም በራስ ጉግሳ ፈርደዋል[42]፤ በሥጋዬ ሊፈርዱ ቢችሉ እንጂ በነፍሴ አይፈርዱም ብለው ፊትለፊት ንጉሡን ገጥመዋል፤ በነገርም ንጉሡን ጎሽመዋቸዋል፤ ቀኛዝማች ምስጋናው አዱኛ።"[43] ሆኖም ግን የስሜንና የቤጌምድር አርበኛ "ለሀገር ክብርና ኩራት ባንድ እጁ መሰንቆ በሌላው ጠመንጃ አፈሙዝ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ ግጥም

---

[38]ሲሳይ ቦጋለ፣ አቶ ዘላለም በቀለ፣ቃለመጠይቅ ቦታ ጠዳ፣ ዕድሜ፣ 62 13/8/2005 ዓ.ም. አስማማው መኮንን፣ቃለመጠይቅ ቦታ ኢንፍራንዝ፣ ዕድሜ 68፣ 13/6/2005 ዓ.ም.
[39] ዝኒከማሁ
[40] ሲሳይ ቦጋለ፣ ዘላለም በቀለ፣ አስማማው መኮንን
[41] ዝኒከማሁ፣ ክብር ይገባዋል ለይሁዳ አንበሳ ለዚህ ንጉሳችን ፣
በድል ተመለሰች እናት ሀገራችን፣ ሞት እንዳገኘህ ሻመት ንገስልን።
[42]ራስ ጉግሳ ወሌ ጋር የነበረውን የሥልጣን ሽኩቻ በአንቺም/ቋና ዘመቻ የተፈታውን ችግር ለማመልከት።
[43] ራዱ ብዙነህ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ጊዜና ቦታ 4/4/2005 ዓ.ም. ጎንደር። በተጨማሪ በሁሉም አለበል፣ 2009 ዓ.ም. ገጽ፣ 83-85 ይመልከቱ።

አስካክ፣ ዜማ በማሳመር ጠላትን በውስጥም ሆነ በውጭ አርበኝነት ሲከራከር፣ ሲታገል ሲያታግል የቆየን ጀግና ሽልማት እንጂ ቅጣት አይገባውም በማለታቸው" ውጥረቱ እንዲረግብ ሆኗል፡፡[44] ሆኖም ቀኛዝማች ምስጋናው በምጸት ትግላቸውን እንዳልተው ቃል መረጃ ሰጪዎች ይጠቁማሉ፡፡[45] እዚህ ላይ ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ "ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ድንቁርና እንዲጠፋ ዋና አሳባቸው ስለሆነ..." ይሉና በዘመናዊ ትምህርት ተቋማት ታንጸው ከወጡት ይልቅ በሀገር በቀል ዕውቀትና ክህሎት የተቃኙትን ለሀገራቸው መስዋዕትነት የከፈሉትን አርበኞች እጅጉን ክብር እንደሚገባቸው ባንድ ወቅት አሳስበው ነበር፡፡ ለምሳሌ፤ ራሳቸው ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ በስደት ጊዜ በአርበኝነት ከንጉሡ ጋር እየተላላኩ እስከ ምድረ ጎጃም ከካርቱም ሱዳን እየተመላለሱ ከእነአርበኛ በላይ ዘለቀ ጋር የትብብር ሥራ ለሀገራቸው ነጻነት ሲሠሩና ሕዝቡን ሲያነቁ ቆይተው ኋላ ውለታቸው በንጉሡ ችላ ተብሏል፡፡ "በስደት ጊዜ የደከምክበትም ሁሉ እንደትንቢት ሆኖ አሁን ደረሰ፤ ዘወትር እናስብሃለን" የተባሉት ዮፍታሔ ወረታቸው አልተመለሰላቸውም፡፡ በተቃራኒው በጠላት ጊዜ ለጠላት አድረው ወገናቸውንና ሀገራቸውን የበደሉት ተሾሙ፤ ተሸለሙ፡፡ የአርበኝነት ሥራ ይሠራ የነበረው ዮፍታሔና መሰል ኢትዮጵያውያን ምናልባት በነበራቸው በሳል አመለካከት ሀገርን ወደተሻለ ብልፅግና ለመውሰድ የሚታትሩትና ባንድም በሌላም መንግሥትን የሚተቹት ተገለሉ፡፡[46]

ከላይ የተጠቀሱትን ትችቶች ወደጎን በመተው ለንጉሡ ገሎ ማዳን በሚመስል መልኩ ጠላት ሀገር ለቆ እንደወጣ ንጉሡም ወደሥልጣን እንደተመለሱ ሊቀመኳሱ እንደገና፤

4) ምነው አንተ ከሳህ ሰው ሁሉ ሲወፍር፤
አንተ ግዛው እንጂ ጠቅል እንደጠፍር፡፡

5) ኃይለሥላሴ ጳጳስ፣
ምነው አንዳንዴ ብትቀድስ፣
ደሳላት ኢትዮጵያን፤
የነፍስ አባቷ ብትሆን[47]፡፡ በማት ተቀኙ፡፡

---

[44] ዝኒከማሁ፣ *ገሪማ ታፈረ ጎንደሬ....*፣ገጽ፣25 እና 241፡፡
[45]ዝኒከማሁ፡፡
[46]ቀኝጌታ ዮፍትሔ ንጉሤ *አጭር የሕይህወትና የጽሐፍ ታሪክ 1887-1939*፣ (አዲስአበባ ፣ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ፣ 2007 ዓ.ም)፣ ገጽ፣174 -178
[47] ሽመልስ ደምሰው

በቁጥር 4 በተመለከተው ግጥም በውስጠ ትርጉም ንጉሠ ነገሥቱ ከምንም በላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቸኛ አማራጭና ለሕዝቡ ከማንም ኢትዮጵያዊ የተሻለ የሚያስቡ፣ ሲታገሉ ከሰውነት ተራ የወጡ ስለመሆናቸው፣ በረከት፣ ምስጋናና ሌሎች ያልሠሩትን አንተ ሠርተሃልና ክብር ይገባሃል፤ ስለበጎ ሥራህ ሌሎችም ይስሙልህ የተባለ በማስመሰል "ምነው አንተ ከሳህ…" እያለ ያላግባብ እንደገለጻቸው ቃል አቀባዮች በስፋት ይተነትናሉ፡፡[48] ሆኖም በተቃራኒው ለሕዝቡ እምብዛም እንደሆኑና ዳግም ለዙፋን መብቃት እንደሌለባቸው ጭምር ግጥሙ ይናገራል፡፡ በተጨማሪም ለሕዝብ ሲሉ የግል፣ የቤተሰቦቻቸውንና የቅርብ ወዳጆቻቸውን ጥቅም የሚነካ ሆኖ ካገኙት ውድቅ የሚያደርጉ ራስ ወዳድ መሆናቸውን የሚያሳይ አስተያየት ከቃል አቀባዮች በኩል በስፋት ይጠቀሳል፡፡[49]

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በቁጥር 5 ግጥም እንደተመለከተው "ኃይለሥላሴ ጳጳስ" ተብለው ንጉሡ ከትልቅ የሃይማኖት አባት ጋር ተነጻጽረው የተቀመጡበትን ሁኔታ እናያለን፡፡ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ነገሥታት ሃይማኖታዊና ዓለማዊ ሕይወትን ባንድ ላይ አጣምረው የያዙ ናቸው ቢባሉም፣ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያንን መሥመር የጠበቁ ቢመስሉም፣ ባብዛኛው ወደ "ዘመናዊው" ዓለም /ምዕራቡ/ አስተዳደራዊ ፍልስፍና ያጋደሉ ተለዋዋጭ ባሕርይ የነበራቸው፣ ሙገሳንና ከንቱ ውዳሴን የሚወዱ፣ ትችትን የማያበረታቱ፣ አንድ ጊዜ ከጠመዱ አስቸጋሪ እንደነበሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡[50] በግጥሙ ይዘትም "ከፖለቲካና ሃይማኖት ጥምረት" ወደሃይማኖቱ እጅጉን ያጋደሉ፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸው፣ የሕዝብን ብሶትና እሮሮ የሚሰሙ፣ የሕዝብ አባትና ነገ በኔ ባይ እንደሆኑ የተገለጸ ይመስላል፡፡ አንዳንዶች ንጉሡ ረጅም የንግሥናና የተድላ ዘመን ያባታቸው መልካም ሥራ ውጤት ነው የሚሉም አሉ፡፡ በተጨማሪም ንጉሡ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን በተመለከተ የሚናገሩት ንግግርና መሬት ላይ በተግባር የሚታየው ተጻራሪ እንደሆነ ይስተዋላል፡፡[51] ሆኖም ግን ንጉሠ ነገሥቱ ከልጅነት እስከ ዕውቀት የሚታወቁት በፖለቲካ መሰሪነት እንደሆነ የጥናቱ ተሳታፊዎች ያስረዳሉ፡፡[52] ከእርሳቸው በፊት እንደነበሩት ነገሥታት የጦር ስልትና ሥልጠና ባይኖራቸውም የተገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም በቀጥታ በውርስ ያላገኙትን የንጉሠ ነገሥትነት

---

[48]ዝኒከማሁ፡፡

[49] ወርቁ ገሠሠ፤ ወ/ሮ ራዱ ብዙነህ እድሜ 81፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ጊዜና ቦታ ጎንደር 4/4/2005፡፡

[50](Bahru,2008)፣ *ፊታውራሪ ተክለሐዋሪያት ተክለማሪያም. ኦቶባወግራፊ (የሕይወቴ ታሪክ)*፣ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣2007 ዓ.ም.)፣ ገጽ፣ 342፡፡

[51]አክሊሉ ሀብቴ፣ *የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ታሪክ የከፍተኛ ትምህርት መቋቋምና መስፋፋት ጉዞ በኢትዮጵያ*፣ (ታይዋን ፕሪንሪነገ ፕረስ፣ 2017)፣ ገጽ፣121፡፡

[52]አቶ ሽፈራው አስረስ ቃለመጠይቅ ቦታ ጎንደር፣ ዕድሜ 72፣ 13/7/2006 ዓ.ም. አቶ መለሰ ቢራራ፣ቃለመጠይቅ ቦታ ጎንደር፣ ዕድሜ 68፣ 11/7/2005 ዓ.ም፡፡

የፖለቲካ ሹመት በጃቸው አስገብተዋል፡፡ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ምንም እንኳን የኢትዮጵያን ዘውዳዊ መንግሥት ሕግጋትን የተከተሉ ቢመስሉም፣ የራሳቸውን ግላዊ ስብእና እንዲጎላ የሚሠሩና ለታማኞቻቸው ብቻ ትልቅ ዋጋ የሚሰጡ ነበሩ፡፡ በንጉሡ አስተዳደር ደስተኞች የነበሩት ጥቅም ተጋሪዎቻቸው ብቻ እንደነበሩም ይገለጻል፡፡ በተለያየ ጊዜ ማእከላዊ መንግሥታቸውን ብቻ ለመጥቀም ታስበው ይወጡ የነበሩ ሕጎችና መመሪዎችን በተመለከተ፣ በፍትሕ መጓደልና በመሳሰሉት ቅሬታውን ሕዝቡ ሲገልጽ ኖሯል፡፡ ሲብስበትም ከመንግሥት ጋር በግልጽም በሥውርም ሲዋጋ መኖሩን የአካባቢው ታሪክ ዐዋቂዎች ያስረዳሉ፡፡ በተለይ ከ1933 ዓ.ም. በኋላ ሥርነቀል አስተዳደራዊ እርምጃዎች መወሰዱ፣ የግብር አከፋፈል ሥርዓት ለውጡ፣ ጉቦና የመሳሰሉት አሠራሮች በሕዝብ ኑሮ ዘንድ ከድጡ ወደ ማጡ በመሆኑ ከፍተኛ ቅሬታን አስከትለዋል፡፡[53]

ከቤተመንግሥት ሥልጣን ሽኩቻ ጋር ተያይዞ የአፄ ኃይለሥላሴን ብልጎት ወደኋላ በመሄድ ከእተጌ ጣይቱ፣ ከበጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት አባት አደር ገዥ ከራስ ጉግሳ ወሌ፣ ከንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሚኒልክ፣ ከልጅ እያሱ ሚካኤል (ወሎ)፣ ከደጃዝማች አያሌው ብሩ የራስ ጉግሳ ወሌ የቅርብ ዘመድ፣ እንዲሁም ከራስ ኃይሉ ተክለኀይማኖት (ጎጃም)፣ ከአድዋው ጀግና ዳጃዝማች ባልቻ ሳፎ እና ሌሎችም ጋር የነበራቸውን ግንኙነትና አሸናፊ የሆኑበትን መንገድ ብዙዎች ያስታውሱታል፡፡[54] በሌላ በኩል ከነጻነት በኋላ ከ1933-1966 ዓ.ም. በሠሯቸው ኢፍትሓዊ ድርጊቶች ይታወሳሉ፡፡ ከጠላት ጋር በመዶለት ባለሟል የነበሩ ሰዎችን ሹመዋል፡፡ በተቃራኒው ከጠላት ጋር ሲከራከሩ የነበሩት በስፋት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ችላ የተባሉበት ጊዜም ነበር፡፡[55] ይህም ብልኀት ለዳግም ዙፋን ያበቃቸው እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ለአምስት ዓመት በዱር በገደል ጣሊያንን ሲከራከሩና ሲዋደቁ የነበሩትን አርበኞች ያስተናገዱበት መንገድ በብዙዎች ይተቻል፡፡ ለአብነት ያህል የቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛትን ብንወስድ አርበኛው ራሱ በጠላት ላይ በሚሠራቸው ገድሎች እየሾመ ራስ፣ ደጃዝማች፣ ባላምባራስ የመሳሰሉትን የማዕረግ ስሞች በመያዝ ሀገሩን ለጠላት ሳይሰጥ እርሳቸው ከስደት ሲመለሱ፣ "እኛ ያልሰጠነው ማዕረግ ከዛሬ ጀምሮ አውርደናል" በማለት ቅር እንዳሰኙት መረጃ አቀባዮች

[53] ዝኒከማሁ፡፡

[54] ዝኒከማሁ፣ ልዑል ራስ እምሩ ኂይለሥላሴ *ካየሁትና ከማስታውሰው*፣ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2009)፣ ገጽ፣ 20 እና 161 ይመልከቱ፤ መርሰዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ 1922- 1927፣ (አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣2009 ዓ.ም.)፣ ገጽ 12-14፤ *አክሊሉ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ታሪክ … ገጽ*፣ 161-62፣ *ዋጋው ቦጋለ፣ ቤተ-ርስት ሥልጣን መዋዕለ-ንዋይ እና በጎአድራጎት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሕይወት (1933-1967)*፣ አሳታሚ የለውም፣2012 ዓ.ም)፣ ገጽ፣ 66፡፡

[55]ዮፍታሔ፣*አጭር የሕይወትና የጽሐፍ ታሪክ … ገጽ፣174፤ ፊታውራሪ* ተክለሐዋሪያት፣ *የሕይወት ታሪክ*….ገጽ፣xvii

ያስረዳሉ፡፡[56] ከላይ እንደተገለጸው፣ በመንግሥታቸውም ከአርበኛውና ሀገር ወዳዱ ይልቅ በርካታ የጣሊያን ባለሟሎች /ባንዳዎች/ እንደነበሩ መናገር ይቻላል፡፡ በጠቅላይ ግዛቱ የነበሩት ውዝግቦች በርካታ መሆናቸውን በዘመኑ የተጻፉ አቤቱታዎችና ክርክሮች ያስረዳሉ፡፡[57]

ከሀገር ወዳድ ባለሥልጣን ሳይቀር ጥያቄ የሚነሳባቸው ለግል ክብራቸው የሚጨነቁ ከንቱ ውዳሴና ትምክህት የተጠናወታቸው በአንዳንድ አጋጣሚ "ኢትዮጵያ ያለ እኔ ምንም አይደለችም፤ እድሏ ከኔ ጋር የተሳሰረ ነው፤ ካለ እኔ ትኖራለች ብለህ አታስብ"፡፡[58] በማለት የሚመጻደቁ እንደነበሩ ያሳያል፡፡ ሕዝብን መርዳትና ብዙሃኑ እንዲለወጥ የሠሩት ሥራ እምብዛም እንደሆነ "ደስ አላት ኢትዮጵያን..." እየተባለ ተሸሚጧል፡፡

6) *መቼ ነግሦ ያውቃል እንዳንት ያለ ንጉሥ*
*አበቃለት ሲባል ዳግመኛ የሚነግሥ*፡፡[59]

በቁጥር 6 የቀረበው ግጥም በተመሳሳይ ለንጉሡ መወድስ ይመስላል፡፡ ሆኖም መንበረ ሥልጣናቸው ላይ የወጡት የውስጥና የውጭ ሁኔታዎች ተመቻችተውላቸው እንጂ እርሳቸው እንደቀድሞ መሪዎች ጠላትን በጦርሜዳ ተፋልመው አልነበረም፡፡ የሕዝብ በተለይ የአርበኛው ተቃውሞም እንደነበረባቸው ይታወቃል፡፡ "ያፈረሰ ቄስ አይቀድስም፤ የተሰደደ ንጉሥ ተመልሶ አይነግስም" ሀገር ለጠላት ለቅቀህ ሄደህ ዳግም ዙፋን ትመኛለህን? የሚል አስተሳሰብም ነበር፡፡ ሆኖም የተገኘው መልካም አጋጣሚ በተገቢው መንገድ ተጠቅመውበታል፡፡ በተጨማሪም ወደ ዙፋን ከመጡም በኋላ ምድር ላይ ያለው ሁኔታ "ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝነሽ ተላላ፤ የሞተልሽ ቀርቶ ያልሞተልሽ በላ" እንዲሉ የአስተዳደር በደል መባባስ፣ ሳይሠሩ ማጌጥ፣ የብልጭልጭ ኑሮ፣ የግል ጥቅም ፈላጊ መብዛት፣ ለኢትዮጵያ መልካም ራእይ ያላቸውን ሰዎች በዘፈቀደ ማጥቃት፣ የፍርድ መጓደል፣ ለእድገት መሠረት የሚሆኑ ተቋማትን የመገንባት ጉዳይ ነጻነትን ዘላቂ ለማድረግ አርቆ አለማሰብ፣ ራስን ለመቻል የሚሠራው ሥራ አናሳነትና ጭራሹንም አለመኖር፣ ለግል ሀብትና ለሥልጣን መስገብገብ፣

---

[56] ወርቁ ገሠሠ፤ ራዱ ብዙነህ፣ ባዩ በዛብህ፣ ምህረቴ ውቤ

[57] አቶ አሊጋዝ የሚባሉ ለጣሊንያ ያደሩና የባንዳ አለቃ የነበሩ ሲሆን፣ በጦር ሜዳ በአርበኞች ተገድለዋል፡፡ ልጃቸው በዛብህ አሊጋዝ የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት መንግሥት ቦታውን ከያዘ በኋላ የሊቦ አውራጃ ምክትል ጸሐፊ እንደሆነና አርበኞችን በቂም በቀል እንዳጠቃቸውና ሲያመልክቱም ሰሚ አለመኖሩን ከቀረቡት ማመልከቻዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ጎንደር መዛግብት ክፍል፣ ፋይል ቁጥር 76/ቤ/ጠ/ ደብዳቤ ቁጥር መ/13፣ ቀን 3/1/55ዓ.ም፤ ፋይል ቁጥር፣ 80/ቤ/ጠ/ ደብዳቤ ቁጥር 3230/60፣ 23/7/1949 ዓ.ም.፡፡

[58] ዝኒከማሁ፣ፊታውራሪ ተክለሐዋሪያት፣ *የሕይወት ታሪክ* ፣ ገጽ፣ xviii

[59] በሁሉም አለበል፣ *ታሪክን በቅኔ ቀኛዝማች ምስጋናው አዱኛ* 2009፣ገጽ 87፤ ራዱ ብዙነህ፣አቡኔ አለማየሁ

ቅኝ ሳንገዛ ነጻነታችንን አጥተን እንድንቀር ሁኔታዎች የተመቻቹ እስከ ሚመስሉ የአመራር ችግር ይስተዋል ነበር። በግል ጥቅምና በሀገር ደኅንነት መካከል በሚነሡ ጉዳዮች ሁልጊዜ ሀገርን ሕዝብን ማስቀደም የሚለውን እሳቤ ንጉሡ የተገነዘቡት አይመስልም። ቢመስሉም በተግባር ማዋልም አልቻሉም። በየመድረኩ የሚናገሩት መልካም ንግግር "የወረቀት ነብር" ሲሆን ይስተዋል ነበር።[60] የሕዝቡን ሀገር ወዳድነት፣ ታማኝነት፣ ሕግ አክባሪነት፣ መከባበር፣ ሆደሰፊነት፣ ጀግንነት የመሳሰሉትን ሥነምግባር ዋጋ እንዲያጡ ሲሠራ፣ በቶሎም ይሁን ዘለቄታዊ ማስተካከያ ሳይወሰድ ሲቀር ሥልጣኔ እየመሰለው ሌላውም ይከተለው ነበር።[61] ሌሎች አንዳንድ የወቅቱ የነበሩ የመንግሥት ባለሥልጣናት አፄ ኃይለሥላሴ የያዙትን አቅጣጫ በመቃወም የንጉሡን አባት ራስ መኮንን እና አፄ ምኒልክን የአስተሳሰብ ልዕልናና ቀናኢነት በማመስገን ቢኖሩ ኖሮ ሀገርና ሕዝብ የተሻለ እድገት ያስመዘግቡ ነበር ብለው ትዝብታቸውን ያካፍላሉ።[62] ስለሆነም ግጥሙ በግነት ያወደሰ፣ ያመሰገነ በመምሰል የንጉሡን ሁለንተናዊ የሥርዓት ችግር ተችቷል።[63] ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤም በነበራቸው የጥበብ ተስጥኦ በመታገዝ "የሰላምና የደስታ መንግሥታችን…." እያሉ በተለያዩ ድርሰቶቻቸውና ግጥሞቻቸው በሽወርኒ የሀገሪቱን ሁኔታና የሕዝቡን ምሬት ሲገልጹ ተስተውለዋል።[64]

በተጨማሪም የንጉሡን አምባገነናዊ አስተዳደር ለማጉላት ቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ ውዳሴ በሚመስሉ ቅኔዎቻቸው ንጉሡ እንከን አልባ መሪ እንደነበሩ በመግለጽ ከላይ በተጠቀሰው ፖለቲካቸው የሚታወቁ መሆናቸውን ጀግና ነዎ! ጣሊያን ሳይሆን አሸናፊ እርስዎ ነዎት እያሉ ንጉሡን የተከራከረ በስቅላት፣ በግዞት፣ ርስቱንም በማጣት ጭምርና በመሳሰሉት ይቀጣ እንደነበር በሚከተለው ቅኔ ተናግረዋል።

7) ዱቼ ሞሶሎኒን ቀጥቃጭ ያለው ማነው

<u>የቀጥቃጮች ቀጥቃጭ</u> ኃይለሥላሴ ነው[65]።

በተጨማሪም በቁጥር 7 በተመለከተው ግጥም ንጉሠ ነገሥቱ ከዓለም አቀፍ አንባገነኑ የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስቴር ቦኔቶ ሞሶሎኒ ጋር ተነጻጽረው ይገኛሉ። በአድዋ ድል በቀል ተነሳስቶ ሉዓላዊነቷ የተከበረውን ኢትዮጵያ በማናለብኝነት በዓለም አቀፍ የጦር ሕግ ጭምር የተከለከለውን

[60]ወርቁ ገሠሠ፤ ራዱ ብዙነህ፣ ባዩ በዛብህ፣ ምህረቴ ውቤ።
[61]ዝኒከማሁ።
[62]ተክለሐዋሪያት፣ ገጽ xxi.
[63]ዝኒከማሁ።
[64] ዮፍትሔ…ገጽ፣ 178-179
[65]አጋፋሪ አበበ፣ ሽመልስ ፣ወርቁ ገሠሠ፣ በሬ ፍሌ

*የመርዝ ጋዝ ሳይቀር በመጠቀም የኢትዮጵያን ሰራዊት ድል ነስቷል፡፡ ሞሶሎኒ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሳይቀር ለአምስት ዓመት የመከራ ዘመን የፈጸመ መሪ ነበር፡፡ የአፄ ኃይለሥላሴም አስተዳደር በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ያልተለመዱ የአስተዳደር ስልቶችን በመዘርጋት ጥያቄ ላነሣ አይቀጡ ቅጣት ቀጪ እንደነበሩ ለማሳየት <u>የቀጥቃጮች ቀጥቃጭ</u> ተብለው ከሞሶሎኒ እንደማይሻሉ ነገር ግን ጀግና ነዎ! ገዳይ ነዎ! ተብሎ ተሽሟጦባቸዋል፡፡*[66]

*እንግሊዞች ጣሊያን ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ፣ እንግሊዞች የኢትዮጵያ የበላይ ጠባቂ ለመሆን እሳቤ ያሳዩ ይመስሉ ነበር፡፡ ይህ ለንጉሡ ሆነ ለአርበኛው የተዋጠ ጉዳይ አልነበረም፡፡ የከፋ ጠብ ሳይፈጠር በስልት እንግሊዞች ኢትዮጵያን ለቀው ይወጡ ዘንድ የዘየዱት ዘዴ ንጉሡ ብልኀተኛ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ከዚህ አንጻር "እሽህን በሽህ" እንዲሉ በተለይ ከአሜሪካ ጋር የጀመሩት ግንኙነት ለዚህ ዲፕሎማሲያዊ ስኬት ንጉሡን አስደንቋቸዋል፡፡*

8) አባ ጠቅል ኃይሌ እጅግ ረቀቀ፤

<u>ነጩን በነጭ</u> ወጋው ማሾ[67] እያጠበቀ፡፡

*የተባለው በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ነው፡፡ የቁጥር 8 ግጥም መልዕክት እንደሚያስረዳው፣ በወቅቱ የኢትዮጵያ ዐቅም እንግሊዝን ለመከራከር የሚያስችል ባይሆንም እንግሊዝ መግፋት እማትችለውን የራሷን ወዳጅና የዓለም ልዕለኀያል ሀገር ዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካን የኢትዮጵያ ወዳጅ በማድረግ የእንግሊዝን ተጽዕኖ መቋቋማቸውና በስልት አሜሪካን ዋነኛ አጋር ማድረጋቸውን <u>ነጩን በነጭ ወጋው</u> እየተባለ የሚያስደንቃቸው እንደነበረ ከሥነቃሉ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህም ከእንግሊዞች ጋር ባስተዳደራዊ ጉዳዮች የከፋ ጠብ ሳይፈጥሩ አስታመው በብልኀት በአሜሪካዊያን ቀይረዋቸዋል፡፡ አንዳንድ የቃል መረጃ የሰጡኝ የታሪክ ዐዋቂዎች የንጉሠ ነገሥቱን ብልኀትና የፖለቲካ ብቃት ሲገልጹት "የተዋጣለት ብልኀታዊ እንቅስቃሴ ይሉታል"፡፡*[68]

---

[66] ዝኒከማሁ::

[67]*ኀይል የሚያመነጭ ቁስ ወይም ሞተር እንደ ማለት ነው፡፡ የንጉሡን ዐቅምና ብልኀት ለማጉላት፡፡*

[68]*አጋፋሪ አበበ አየለ፣ ልዑል ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ፣ ካየሁት ከማስታውሰው፣* 2008 *ዓ.ም.፣ ገጽ* 303፤ *አክሊሉ ሀብቴ የከፍተኛ ትምህርት….ገጽ፣* 124፣142፤ Harold G. Marcus, The Ango- Ethiopia treaty of 3January 1942: Did Etyhiopia became a British Protectorate ? *Proceeeding of the XIV[th] International Conference of Ethiopian Studies*, Baye Yimam et al. (ed. ) Vol. I (Addis Ababa Uiversity, 2000), pp .414-21.

9) ጣሊያን መንገድ ሠሪ እንግሊዝ መሪ ነው

ጠቅልሎ የሚገዛው ኃይለሥላሴ ነው፡፡[69]

የአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን በአንጻራዊነት የተረጋጋ፣ ረጅምና ዓለም አቀፋዊ ተሰሚነቱ መልካም የሚባል ነበር፡፡[70] በተለይ በጣሊያን ወረራ የተነሣ በአውሮፓውያን ፊት ቆመው በሀገራቸው የአማርኛ ቋንቋ የተናገሩት ንግግር ዓለምን ያስገረመና ትንቢተኛው ንጉሥ የተባሉበት አጋጣሚ ነበር፡፡ ኢፍትሓዊ ወረራውን ኀያላን ሀገራት በዝምታ በማለፋቸው የተነሣ የተናገሩት ንግግራቸው "ጓደኛህ ሲታማ ለኔ ብለህ ስማ" እንደሚባለው ሆኖ መገኘቱ ደግሞ በዓለም ሕዝብ ዘንድ ከበሬታን አጎናጽፏቸዋል፡፡ ንግግራቸውን ተከትሎ ብዙም ሳይቆይ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአውሮፓውያን መካከል ተጀመረ፡፡ በዚህም ኢትዮጵያን በግፍ የወረረችው ጣሊያንና ግብረአበሮቿ ጀርመንና ጃፓን ባንድ ወገን እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ሩሲያ በሌላ ወገን ሆነው ደም ተፋሰሱ፡፡ በጠብ ጫሪነት የሚጠቀሰውም የኢጣሊያ፣ ጀርመንና ጃፓን ካመፕ ነበር፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ከነጻነት በኋላም ከ1936-1966 ዓ.ም. በፍጹም ማእከላዊ አስተዳደር ምሥረታ ጠንካራ እንደነበሩ ታሪክ ያስረዳል፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክም ከየትኛውም ንጉሥ በተሻለ መልኩ ማእከላዊ ግዛት የነበራቸው እርሳቸው ነበሩ፡፡[71] ለምሳሌ፤ ከእንግሊዝና አሜሪካ ጋር በነበረው የውጭ ግንኙነት ንጉሡ ተቀባይነታቸው ጥሩ እንደነበር የታሪክ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡[72] በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የጣሊያንን ሽንፈት ተከትሎ አጋጣሚውን በአግባቡ በመጠቀም ወደ ዙፋናቸው ተመልሰዋል፡፡ "ያፈረሰ ቄስ አይቀድስም፤ የተሰደደ ንጉሥ ተመልሶ አይነግሥም" ሀገር ለጠላት ለቀህ ሄደህ ዳግም ዙፋን ትመኛለህን? በማለት የተቃወማቸውን አርበኛ ባግባቡ ውጥረቱን አርግበዋል፡፡ ለዚህም የእንግሊዞቹ እርዳታ ቀላል አልነበርም፡፡ አንድ ነገር መታወቅ ያለበት እንግሊዞቹ ይህን ያደረጉት ንጉሡን ወደው አይመስልም፡፡ ሆኖም ግን ለእንግሊዞቹ ንጉሡ "ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን" እንደሚሻሏቸው እርግጠኞች ስለነበሩ ይመስላል፡፡ ከአርበኞቹ ቀላል የማይባል ተቃውሞ

[69] ወ/ሮ ሙሉ ወርቃየሁ፣ ዕድሜ 63፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ ጎንደር፤ 2/9/2005 እና 4/10/2007፤ ሽመልስ ደምለው፡፡

[70]አክሊሉ ሀብቴ፣ *የከፍተኛ ትምህርት….ገጽ*፣304፡፡

[71]Bahru Zewde and Siegfried Pausewang (ed.), *Ethiopia : The Challenge of Democracy from Below*,*Forum for Social studies*(Addis Ababa,2006), p.10.

[72]ወረቁ ገሠሠ፣ አበበ ማለደ፣ አበበ አየለ፤ Bahru Zewde*, AHistory of Moden Ethiopia 1855-191*,(Addis Ababa University Press, 2001), p. 205,pp.179-189.

እንደሚያጋጥማቸው ልቦናቸው ሳይረዳው እንዳልቀረ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡[73] ለዚህም ትልቅ ማስረጃ "የነጭ ነጭማ ምን አለን ጥሊያን"[1] የሚለው የአርበኞች የጀግንነት ቃል ጥሩ ምሳሌ ነበር፡፡[74] ንጉሠ ነገሥቱ እንግሊዞችን በተመለከተ ይከተሉ የነበረው "approach-aviodance"/ "መውደድም መጥላትም"/ የሚመስል ስልት ሲሆን፣ ባጭሩ ይወዷቸዋል፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ወደሥልጣን እንዲመጡ ስለረዷቸው፣ በተቃራኒው ደግሞ እንግሊዞቹ ለንጉሡ እማይገፉት ጠላት ሆነውባቸው የቆዩበት ሁኔታ ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያታቸው "የጠላት ግዛት" በሚሉት የቀኝ ግዛት የማስፋፋት ዓላማቸው የሀገሪቱን የረጅም ጊዜ የነጻነት ታሪክ ለማኮላሸትና የጣሊያንን የይስሙላ የአምስት ዓመት ቆይታ እንደቅኝ ግዛት መውሰዳቸውና ጣሊያን ድል ሆኖ ከወጣ በኋላ ለኢትዮጵያ ነጻነት ዕውቅና ለመስጠት ችላ ማለታቸው ዋነኛው ጉዳይ ነበር፡፡ ለምሳሌ፤ የንጉሡ ቃል እንደሚከተለው ይነበባል፡፡ "በኛ በኩል ሀገራችን አማካሪ እንደሚያስፈልጋት እናውቃለን፤ ነገር ግን ነጻነቷ ሳይነካ ካልሆነ፣ ከጣሊያን ቀንበር ወጥታ ወደ ሌላ ቀንበር ትዞራለች ማለት የማይታሰብ ከንቱ ነው፡፡"[75] "መቼ መጣች ሙሽራ፤ ምን ቀረጠመች ሽንብራ" እንዲሉ እንግሊዞች ለንጉሠ ነገሥቱም ሆነ ለሀገሪቱ ሕዝብ እምብዛም ሆድ ሚያስነፉ ወዳጅ አልሆኑም፡፡ ምንም እንኳን ቀጥሎ ባለው አንቀጽ እንደሚነበበው በ1932 ዓ.ም. ንጉሡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጻፍት ደብዳቤ ስለእንግሊዞች ታማኝነት ደጋግመው መስክረው ነበር፡፡ በመሰሪነት ሕዝቡ ከጣሊያን ይልቅ የሚያስታውሰው እንግሊዞችን ነው፡፡ ከመምጣታቸው የሀገሪቱን ሁሉንም ነገር በእጃቸው አስገብተዋል፡፡ ለምሳሌ፤ እንደጦር ኀይል ያሉትን ቁልፍ ቦታዎች፣ ጣሊያን የገነባቸውን ፋብሪካዎች፣ የኢንዱስትሪ እቃዎችንና የመሳሰሉትን በማንአለብኝነት ተቆጣጥረው ነበር፡፡ ጎንደር አንዱ የጣሊያን የጦረ ኀይል፣ ፖሊቲካም ሆነ ኢኮኖሚ ማእከል ስለነበር ጣሊያን ያከማቸውን ንብረት እንግሊዞቹ ወደአሥመራና ናይሮቢ (ኬኒያ) አግዘዋል፡፡[76] በተለያዩ ትንታኔዎች እንደተረዳነው ንጉሡ በትዕግሥት ምላሽ ለመስጠት ጥረት አድርገዋል- ስኬታማም ነበሩ፡፡

---

[73]ጥሩነህ ዜና፣"የኢትዮጵያ ዘመናዊ ድፕሎማሲ አጀማመርና ሂደት (ከነጻነት እስከ አብዮት)"፡፡ *የማኅበራዊ ጥናት መድረክ፡ ከድህነት ወደ ልማት፦ ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ ሁለተኛ እትም፣ ቁጥር ስድስት፡፡* (ማኅበራዊ ጥናት መድረክ፣ 2000)፣ገጽ 1-16፡፡

[74]ወረቁ ገሠሠ፣ አበበ ማለደ፣አበበ ሽመልስ ደምለው፡፡

[75]Bahru Zewde, *Society State and History Selected Essays*, (Addis Ababa University Press,2008),pp.166-172).

[76]ስለሺ ደምለው፣ ራዱ ብዙነህ፣Bahru 2008, pp, 166-167; Debash Yimam. (2011). "The History of Wagara Warada to 1974".(M.A Thesis in History A.A.U, 2011),pp,101፣ጥሩነህ፣ 2000፣ገጽ፣ 1-16 )፤Girma Tayachew, "The

በተመሳሳይ እንደቃል አቀባይዎቼ አገላለጽ ከሆነ ከላይ የተጠቀሰው ግጥም ንጉሡ በዚያ አስቸጋሪ ዘመን ወደ መንበረ ሥልጣናቸው የመጡበትን የፈተና ዘመን ያስታውሰናል፡፡ ከውጭ እንግሊዞች፣ ከውስጥ አርበኛውን ያስተናገዱበት ዘዴ የሚያስደንቃቸው ይመስላል፡፡ ለምሳሌ፤ *መጀመሪያ* አካባቢ እንግሊዝን እንዴት እንደተጠቀሙ በ1932 ዓ.ም. ሐምሌ 1 ቀን ከእንግሊዝ ጦር ጋር ከሎንደን ካርቱም ሱዳን እንደገቡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በላኩት ደብዳቤ፤

> *.... ሹማምንትና አርበኛ....የመዳኛችሁ ቀን ደረሰ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ የታላቂቱ ብሪታኒያ መንግሥት ነጻነታችንን በሙሉ እንድናገኝ ተወዳዳሪ የሌለው ጦር ኀይሉን እርዳታ ሰጠን፡፡.......በታላቂቱ ብሪታኒያ መንግሥት እርዳታ ሀገራችንን በማደስና በማሰልጠን የሚገኘውን ፍሬና ደስታ ተካፋዮች ትሆናላችሁ፡፡ .....ታላቋ ብሪታኒያም ታደርግልን የተገባንን ሆነን ለመገኘት እንወቅበት፡፡ የጋራ ጠላት የሆነውን ጣሊያንን ለመደምሰስና የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት መልሶ ለማቋቋም ነው እንጂ እንግሊዞች ሀገራችንን የሚፈልጉብን ነገር የለም፡፡ ...... በማንኛውም ቦታ .... በወዳጅነት ተቀበሏቸው.....፡፡*[77]

ብለው የላኩ ሲሆን፣ በሂደትም ከላይ "...ነጩን በነጭ ወጋው..." እንደተባለው የሚያስደንቅ ሥራ ሠርተዋል፡፡ ለግዛት አንድነት የሠሩትን ብስለት የተሞላበት የዲፕሎማሲያዊ ጥረታቸውን ለመዘከርና ለማወደስ የቀረበ እንደሆነ ቃል አቀባዮቼ ያስረዳሉ፡፡[78] ከጎረቤት ቅኝ ገዥዎችም ጋር በተለይ ከእንግሊዞቹ ጋር በመደራደር በምሥራቁና በሰሜኑ ክፍል የነበረውን የግዛት ሽኩቻ ለኢትዮጵያ እንዲፈረድ አድርገዋል፡፡ እዚህ ላይ የአሜሪካ እርዳታ ቀላል እንዳልነበር መረጃ ሰጪዎቼም ምሁራንም በጥልቀት ያስረዳሉ፡፡[79] ጣሊያንንም እንግሊዝንም በአግባቡ አስተናግደው የኢትዮጵያን ግዛት እስከ ቀይ ባሕር መለስ አድርገዋል፡፡[80] ሆኖም ግን ከዚህ ጽሑፍ አንጻር "ጠቅልሎ እሚገዛው ኃይለሥላሴ ነው" የሚለው ሐረግ በግጥሙ ውስጥ እንመለከታለን፡፡ በቁጥር 9 ግጥም እንደተጠቀሰው ይህ የጥንካሬ ምልክት ቢመስልም የሀገሪቱ የውስጥ ሁኔታዎችም ሆኑ የውጭ ጥሩ እንዳልሆኑ ይጠቁማል፡፡ ነባሩን አሠራር ለማስቀጠል በሚተጉ

Administration of Italian buildings and holdings in Gondar Town 1941-1974" ,*EJSS* ,Vo.3,2017,p.13.

[77] *ገሪማ ታፈረ፣ ጎንደሬ በጋሻው...*ገጽ፣ 236-238፡፡

[78] አበበ አየለ፣ ሽመልስ፣ ዋኘው ዘርጋው

[79] ዝኒከማሁ፡፡

[80] ዝኒከማሁ፤ (ጥሩነህ ፣2000፣ገጽ፣ 1-16) በተጨማሪ ይመልከቱ፡፡

ወገኖችና በለውጥ ፈላጊዎች መካከል ያለ ሥርዓት መሆኑንም ያሳየናል፡፡[81] ይህም ረጅሙን የንጉሡን ዘመነመንግሥት የሚጎዳ መሆኑን ሕዝቡ ይረዳው እንደነበር ማየት ይቻላል፡፡

10) በዚህ በዚያ ብሎ ካላሉት ሆይ ሆይ፤
<u>አልጋው ቀዳዳ</u> ነው ያስበላል ተባይ፡፡

11) ተፈሪ መኮንን አልጋው ደህና ሳለ <u>አሽከር</u> ሳይሰፍርበት
ልጆቹን ቢተካ እንዴት ባማረበት፡፡[82]

በቁጥር 10 ግጥም የተመለከቱት ስንኞች የንጉሠ ነገሥቱ ገደብ የለሽና የዘፈቀደ አስተዳደር ገደብ እንዲኖረው፣ ለውጥ እንደሚያስፈልግና የሕዝብን ድምፅ መስማት የግድ እንደሚለው፣ መንግሥትና ባለሚሎቹ የሕዝብ አገልጋይነት አስተሳሰብ በውስጣቸው እንዲሰርጽ ግድ መሆኑን ያሳስባል፡፡ እዚህ ላይ አንድ ለሁለንተናዊ ፍትሕ ይታገሉ የነበሩ የኢትዮጵያ ድፕሎማት ያሉትን መጥቀሱ የሚስፈልግ ይመስለኛል፡፡ "....አልጋ ወራሽ የኔን ሐሳብ የነቀፉ ሆነው የራስ ካሳን ቢከተሉ፣ የማንኛችን ትክክለኛ መሆኑን የሚረዳ ማነው? መጪው ጊዜ ብቻ ያስረዳናል፡፡ እኛ ብንሞትም እንኳ የኢትዮጵያ ትውልዶች ያገኙታል"[83] - ብለው ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚታዩት ሁለንተናዊ ችግሮች ባሉበት ቀጥለው ለንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን አስጊነታቸውን በማሳየት "<u>አልጋው ቀዳዳ ነው</u>" በማለት መልካም የሚባሉ ሁኔታዎች እንደሌሉ የሥርዓቱ ክፍተቶች በርካታ መሆናቸውን በግልጽ የለውጡን አይቀሬነት ለማሳየት የሞከረ ይመስላል፡፡ የመጨረሻዎቹ በቁጥር 11 የተመለከቱት ስንኞችም ምንም እንኳን ንጉሡ ከተራማጅ ወገን የሚመደቡ ናቸው ተብሎ ቢነገርላቸውም፣ ራሳቸውም ሆኑ ወዳጆቻቸው ግለኝነትና ወግ አጠባቂነት ባሕሪያቸው እንደነበር ከተግባራቸው መመልከት ይቻላል፡፡ የተለያዩ የመንግሥትና የግል ተቋማትን በመጠቀም ለምሳሌ፤ በቤተርስት ጽሕፈትቤት፣ ጽሕፈት ሚኒስቴርንና ሌሎችንም በመጠቀም የግል ሀብት ማካበትና ለሥልጣናቸው የነበራቸውን ስስት[84] ከታማኞቻቸው ጋር በመሆን እስከ መጨረሻው ለማትረፍ መጣር እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለተናዊ እጣ ፈንታን አላዩትም ወይም ሌሎች እንዲያሳዩዋቸው ፈቃዳቸው አልነበርም፡፡ ስለሆነም የንጉሡንና የሥርዓታቸውን ማርጀትና ማፍጀትን በመጥቀስ ለቀጣዩ ትወልድ ችግሮች ከመፈጠራቸው በፊት ንጉሡ ሥልጣን ቢያስረክቡ መልካም እንደሚሆን ስንኙ ይመክራል፡፡ የመንግሥት አወቃቀሩ ሳይቀር

---

[81](ወ/ሮ) ስትና ሙስጦፋ፣ (አቶ) ምህረቴ ውቤ፣ (አቶ) መሐመድ አማን
[82] ሲሳይ ቦጋለና ይመር እምሩ ፡፡
[83]ፊታውራሪ ተክለሐዋሪያት ኦቶባዮግራፊ...ገጽ፣ 344፡፡
[84] ዋጋው፣ ገጽ፣ 116፣120 እና 329፡፡

መቀየር አለበት የሚል የፖለቲካ ትንታኔ ከማኅበረሰቡ ተወካዮች ይቀነቀን እንደነበር መረጃዎች አሉ፡፡[85]

12) በሬና ገበሬ ያርሳሉ ተራምደው፣
ወንዙን ሸለቆውን ተራራውን ዞረው፣
የጃንሆይ መንግሥት ማር ነው ወለላ ነው፡፡

13) አንቺ ለምንድነው በሩን የዘጋሺ
ባላገሩ ከፍቶት ሲያድር እያየሺ፡፡[86]

ግጥም 12 የሚያስረዳን በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የነበረውን የገበሬውን ሕይወት የሚያሳይ ሳይሆን አይቀርም፡፡[87] አዎ! ገበሬው ጋራ፣ ተራራ ዞሮ ያርሳል፤ ይለፋል፡፡ "ገባር የሚበላው እንጂ የሚከፍለው አያጣም" እንደሚባለው እርቦ፣ ዐስራት፣ ምልምል፣ የጢስ ግብር፣ የጢስ ጨው[88]፣ የጥሎሽ ማር፣ የበሬ ጫንቃ፣ የመልማይ እራት፣ ያመት ባል መዋያ፣ የባሕርይ መግዣ፣ የበር ከፋች፣ የጭቃ ቆሎ[89]፣ የደንበኛ፣ የዘላን ግብር፣ የፈረሰኛ፣ የጉልበት ዕዳ፣ የጭቃ ማር፣ የትምህርት፣ የጤና ግብር፣ የአሞራ ግብርና ሌሎችንም እንዲከፍል ይደረጋል፡፡[90] ክፍሎም በማኅበራዊ ልማቶች ተጠቃሚ አልነበረም፡፡ አርሶ ምን ያክል ከምርቱ ተጠቃሚ ነበር? ምን ያህል ይለፋ ነበር? ማረስና ማምረት ብቻ የገበሬውን ኑሮ ይለውጣልን? "ተያየን ተለያየን"[91] ምርቱን ያየዋል "ለባለመሬቱ" ለተሠሪው

[85] ሲሳይ ቦጋለና ይመር እምሩ ፡፡
[86] ወ/ሮ ሀዋ አብዱረህማን ዕድሜ 53፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ፤ መተማ 2/9/2005 እና 11/-13/11/2006
[87] ወርቁ ገሠሠ እና ሽመልስ ደምለው
[88] ዝኒከማሁ፡፡
[89] ሌቱን ቀኑን ሠርተን ያመረትነውን፣
ጭቃ ሹሙ መጥቶ ጭቃ ቆሎየን፣
ፈረሰኛው መጥቶ ስጡን አምሻየን፣
በላባቱም መጥቶ ለኔም አበሌን፣
ተካፍለው ወሰዱት ያመረትነውን፣
እኛም እያለቀስን ወደ ቤታችን፡፡
[90] ዝኒከማሁ፣አበበ ማለደ ፣Debash, 2011, p.102; Ayichew Adisu,"Geledeba and Aykel the twin Towns of Chilga 1270-2000." (B.A Thesis, AAU, 2001), p.28.

[91] ታገኝ ወርቁ ዕድሜ 58 ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ፤ ኢንፍራነዝ 2/1/2005 እና 1/4/2007፤Teshale Tibebu, *The Making of ModernEthiopia 1896-1974*, (Red Sea Press, 1995) p.72.

ይሰጣል፡፡[92] የበልግ እርሻ ሳይቀር ገበሬዎች አስራትና ሌሎች ጫናዎችን እንዲከፍሉ የሚጠየቁበትም አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ ደባሽ ይማም ይህን በተመለከተ በደጃዝማች አያሌው ብሩ አስተዳደር ጊዜ ብላታ ገ/ሕይወት የተባሉ ገበሬ በወገራ አካባቢ በአንድ መሬት ሁለት ጊዜ አስራትና አምሾ ይከፍሉ ዘንድ በመጠየቃቸው ጉዳዩን እስከ አዲስ አበባ ንጉሥ ችሎት እንደወሰዱት ይነግረናል፡፡[93] በቁጥር 13 የተመለከተው ግጥም በተመሳሳይ የተነሡት ጥያቄዎች ምሬትና ተስፋ መቁረጥ ከገበሬው አእምሮ ውስጥ እንደሚመላለሱ ገጣሚው ለማሳየት የሞከረ መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ስንኝ ሊገለጽ ያሰበው ጉዳይ ሀገር ሰላም ነው ለምን ቅሬታ ይሰማናል? በቀጣዩ ስንኝ ግን <u>ከፍቶት</u> የሚለው ድብቁ ትርጉም ሰላም የለም፤ ገበሬው ቆዝሞ ከፍቶት ኑሮውን እየመራ ነው ለማለት የተገጠመ መሆኑን እናያለን፡፡[94]

14) ግርማዊ ጃንሆይ በጣም ጻዲቅ ነዎ፣
እየሱስ ስራዎን የገለጠልዎ፡፡[95]

በዚህ ቁጥር 14 የተጠቀሰው የቃል ግጥምም እንዲሁ ስለ ግርማዊ ጃንሆይ አመራርና አስተዳደራቸው ላይ የነበሩትን ክፍተቶች ይነግረናል፡፡ እንደቃል መረጃ ምንጮቼ ትንተና፣ ያስተዳደር በደል፣ የፍርድ መጓደል የምጣኔ ሀብት /የኢኮኖሚ ድቀት እጅጉን ያሳሰባቸውና ለኢትዮጵያ ትንሣኤ መሥዋዕት ለመሆን የደረሱ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ሳይቀር ያነሡት የነበረውን የሥርዓት መሻሻል ጉዳይም በዚህ ይዘት ውስጥ

---

[92]የገበሬውን የአስተዳደር ቀሬታ በተመለከተ Gebru Tareke,*Peasant Revolts in the Twentieth Century*(The Red Sea Press.1996),pp. 3-128,);Dessalegn Rahmeto the Pseant and the State : Studies in the Agrarian change in Ethiopia 19505-2000s (Adis Ababa University Press, 2009),p.286

[93] Debash, p.35፣ ከዚህ ጋር በተገኛኘ፤ በዘረፋ ገንዘብ ቤት ውስጥ ተሞሽሮ፣
እስከ መቼ ድረስ በደል ይስማ ጆሮ፣
ይደንቁር በሮሮ
ተራው ሕዝብ ሲሰደድ ባገዛዝ ተማሮ
አሮበት አሻሮ
ድህነት ከራሱ እንደ ጠጉር ሰፍሮ፡፡ እየተባለ ከአምደኞች የሁኔታውን ክፋት ይዘገብ ነበር፡፡ ትይንተ ጎንደር፣ 1966፣ ገጽ፣ 2-3

[94]እዚህ ላይ የነበረውን በደል በመፍራት ጭሰኞች ሳይቀሩ ያላቸውን ንብረት ለግርማዊነታቸው በቤተርስት ጽሕፈትቤት ያወርሱ ነበር፡፡ ይህም በዋናነት ንጉሡን ወደው ሳይሆን ከነጣቂ፣ ከጉልበተኛ ጥላ ከለላ ይሆናል ብለው በማሰብ ይመስላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የዶ/ር ዋጋውን ትንታኔ መመልከቱ በቂ ይሆናል (ዋጋው፣ ገጽ፣65 86-89 እና117 ይመልከቱ)፡፡

[95] ወ/ሮእራዱ ብዙነህ እና በሬ ፍሌ

እንደሚነበብ ይጠቁማሉ፡፡ ምንም እንኳን ንጉሠ ነገሥቱ በጎንደር ቤተመንግሥት እንኳን ሳይቀር የንጉሥ ችሎት በማዘጋጀት ከጠረፍ አካባቢ ካሉት የሀገሪቱ ሕዝቦች በመጀመር እምነት ቋንቋ ሳይገድባቸው እስከ መኳንንቱና መሳፍንቱ ስለሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ  እንዲናገሩ ያደርጉ ነበር፡፡ መሠረታዊ ለውጥ ግን ሊያመጣ አልቻለም፡፡ ንጉሡ በንግግራቸው ኢትዮጵያ ወገን ያልተለየባት አንድ ቤተሰብ ሆና ሕዝቡ በአንድ ሕግ ተወስኖ በአንድ ንጉሠ ነገሥት ተገዝቶ በመተባበር ለዘለቄታው ጥቅሙ ተጠብቆለት እንዲኖር ምኞታቸው እንደነበር በተለያዩ መረጃዎች ተገልጧል፡፡[96] ሁኔታውን ለመቀየር ንጉሠ ነገሥቱ የሚፈቅዷቸው የመንግሥት ባለሟሎቻቸው ሳይቀሩ ለለውጥ የተነሣሡበት አጋጣሚ ነበር፡፡ ለአብነትም የ1953 በእነኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ፣ በንዋይ ወንድማማቾች፣ በኋላም በ1962 ዓ.ም. በእነደጃዝማች /ብላታ/ ታከለ ወ/ሐዋርያት፣ እንዲሁም በእነልዑል ራስ እምሩ[97] የተሠሩት የለውጥ ፋና ወጊ ተግባራት ምናልባትም ከ1966 ዓ.ም. ከተካሄደው አብዮት የተሻለ ብርሃን ለማምጣት የተደረጉ ጥረቶችን የዘከረ ነበር፡፡ ሆኖም ግን የሚፈለገው ለውጥ በቀላሉ ሳይመዘገብ ቀርቶ እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሱ እንዲቀጥል ሆኗል[98]፡፡ በመጨረሻም ንጉሡ የሕዝቡን ችግር ለመፍታት ባለመቻላቸው እርሳቸውን “ግርማዊ ጃንሆይ … እየሱስ ሥራዎን …” በማለት እንደችግር ፈች ቢወሰዱም፣ በተቃራኒው እንደሆኑና በመሳፍንቱና በመኳንንቱ ጫና ሥር የወደቁ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው፡፡ ለምሳሌ፤ ትይንተ ጎንደር የተሰኘ መጽሔት  ዘመኑን ለመግለጽ እንዲህ ይላል፤

> በመሬት ጫንቃ ላይ ታዝለን የምንኖር ሁሉ ለዚች ለተሸከመችን ምድር ውለታ ለመመለስ ያክል አንዳንድ ነገር ሠርተን ለማለፍ ይገባን ነበር፡፡ ነገርግን በአንዳንድ ግብዞች የሥጋ ፍላጎት የተነሣ እንዳንናገር ተለጉመን፣ እንዳንሠራ እጃችን በክብር ሰንሰለት ታስረን፣ እንዳንሄድ በኀይል ካስማ ተቸንክረን፣ እንዳናይ ዐይናችን በመጋረጃ ተሸፍኖ እነሆ ለብዙ ዘመናት የሕይዋን በድን ሆነን ቆይተናል፡፡ በገዛ ሰማያችን ላይ ለጥቂቶች የተዘረጋውን ድሎትና

---

[96]አክሊሉ፣ *የከፍተኛ ትምህርት* ገጽ፣121

[97]ልዑል እምሩ *ካየሁትና* ገጽ፣320፤ ብርሃኑ አስረስ፣ *ማን ይናገር የነበረ የታኅሳስ ግርግርና መዘዙ*፡፡ (አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣2005 ዓ.ም.)፡፡

[98]Bahru Zewde, *AHistory of Modern Ethiopia*....,p. 205፣ መስፍን ሀይሉ፣*አደራ!ኢትዮጵያን በደማቸው ያስጠበቁ ጀግኖችና የጀግንነት ግጥሞች*፡፡ ማንኩሳ አሳታሚ፤ አዲስአበባ፡፡ 2002፤ ገጽ 196፤ Markakis, J. & Nega Ayele.(1977).*Class and Revolution in Ethiopia*. Review of African Political Economy 1977), pp. 3-79 ይመልከቱ፡፡

ትፍሰህት ስንመለከት … አእምሯችን በከንቱ ፍልስፍናቸው ሰክሮ ….እንደአማልእክት ስንቆጥራቸው ኖርን፡፡…[99]

እያለ የነበረውን የፍርድ መጓደልንና የአስተዳደር በደልን ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም ቀኝ ጌታ ዮፍትሔ ንጉሤ በበኩላቸው "ለስማችን ሞገስ ለደጉ ተፈሪ ጥበብ ተሰጥቶታል ተላይ ተፈጣሪ"፡፡ እያሉ ንጉሡን በሽወርኒ የገለጹበት መንገድ ርእሰ ጉዳዩን የሚያግዝ ይመስላል፡፡[100] ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢም ሆነ በሌላ የሀገሪቱ ክፍል ጥያቄዎች ለንጉሥ ችሎትም ይሁን ለሌላ የመንግሥት አካላት ሲቀርቡ መፍትሔ አለመኖሩን ያሳየናል፡፡ ለዚህም ይመስላል ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ የንጉሡ የክብር ዘበኛ ኀላፊ በ1953 ዓ.ም.[101] ባልተሳካው መፈንቅለ መንግሥት ማግስት በመፈንቅለ መንግሥቱ ለሞቱት መኳንንቶች ንጉሠ ነገሥቱ ሲጠይቁት "ምነው ልጆቼ እንዲህ ታደርጋላችሁ?" ሲሉት "ምን አደረግን? ሽክምዎትን አቃለልን እንጂ……" ብሎ መሳፍንቱ የሥርዓት መሻሻል ጥያቄ ጥቅማቸውን እንደሚያስቀርባቸው በማሰብ በዐይነ ቁራኛ የሚያዩ እንደነበሩ ተናግሯል፡፡ ሥርዓቱም በሂደት ችግር ውስጥ እየወደቀ መምጣቱን ያሳየናል፡፡[102] ለዚህም ይመስላል፣

15) ዘንድሮ ጎጆዬን አምባ ላይ ሠርቻት፤
ሞቅ አለች ሞቅ ሞቅ ስፍራው ተመችቷት፡፡
16) ትልቅ ሰው ሲናገር የለበትም ውሸት
የተፈሪን አልጋ ተማሪ ጣለለት፡፡

በቁጥር 15 የተጠቀሰው ቃል ግጥም የንጉሡን ሥርዓት አለመረጋጋትና ጽኑ መሠረት ላይ ያለመሆን ጉዳይ የዳሰሰ ነው፡፡ ይህንም "ስፍራው ተመችቷት" እያለ ያሸሟጥጣል፡፡ የወደፊት ዕጣ ፈንታውም ምን

---

[99] ጎንደር ከተማ ማዘጋጃ፣ *ትይንተ ጎንደር መጽሔት*፣1966 ዓ.ም.፣ቁጥር 11፣ ገጽ፣1.
[100]ዮፍትሔ…..ገጽ፣ 52 እና 156 በተከታታይ እንደምናየው የአርበኝነት ኑሮን ምናልባት ኑጉሡ በሀገራቸው ቆይተው ጣሊያንን ቢከራከሩ የሀገራቸው ሕዝብና ተራራ፣ ደን፣ ሸለቆ እንደማያስነካቸው ለመናገር፤ "አንተ አታውቅም እንጂ ሹልክ ያለች ኑሮ፣ ማን ያወጣህ ነበር ከሆዴ በርብሮ"፡፡ "ዋርዳና ሳሙና አስሬ ከቤቱ፣ ሳይህ ፈረስ ፈረስ ይላል ሰውነቴ"፡፡ በማለት በሚስጢር እንደተቸ ይነገራል፡፡
[101](ስለሽ ደምለው፣ በሁሉም አለበል፣ 2009 ዓ.ም. ይመልከቱ)

ንፋሱ ነፈሰ የለኝ መጋረጃ
ልብስም አልገዛሁም ምክንያቱን እንጃ፡፡
እንዲህ በታህሳስ ብንሰማ ወሬ፣
አላውቅም ብየነው አለመናገሬ፡፡

[102] አበበ ማለደ፡፡

እንደሚሆን ለማሳያ የቀረበ ሳይሆን እንዳልቀረ የቃል መረጃ ሰጪዎቹ ይጠቁማሉ፡፡ ይህም በወቅቱ ሀገራዊ አጀንዳ ናቸው ከተባሉት የተማሪዎች ንቅናቄና የገበሬዎች ዐመጽ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ግንዛቤ መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ በቁጥር 16 የተመለከተው ግጥም የንጉሠነገሥቱን ሥርዓት ለማስተካከል  የተማሪዎችን ዘርፈብዙ ንቅናቄ ያሳየናል፡፡ የተማሪዎች ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋምና መሬት ላራሹ ንቅናቄዎች ከመፈንቅለ መንግሥቱ በኋላ እየተጠናከረና እየተባባሰ መምጣቱ ለለውጡ ዋነኛ ምክንያት መሆኑን ቃል መረጃ ሰጪዎች ይተነትናሉ[103]፡፡ የደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋሪያትና የተማሩት ወገኖች የለውጥ ሙከራም እንዲሁ ሀገራቸው በታሪክ ቀዳሚነቷ ቀድማ መገኘት ሲኖርባት በቅርብ ከቅኝ ግዛት ነጻነታቸውን ያገኙት የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ስትነጻጸር በማንኛውም ረገድ ኋላቀር ሆና መገኘቷ ቁጭት በማሳደሩ፤ የተሻለች ኢትዮጵያን ከመፍጠር አንጻርና የሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ በሂደት ተረክበው ወደአደባባይ እንዳወጡት በስንኞቹ ዙሪያ ሐሳብ የሰጡኝ የዕድሜ ባለጸጎች ይተነትናሉ፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ የተለያዩ ጥያቄዎች በማንገብ የተማሪዎቹ የለውጥ እንቅስቃሴ ያልተደፈረውን ደፍረው ያስወገዱት እነሱ ናቸው፡፡ “ተማሪ ጣለለት” የሚለው ቃል ሁለት ትርጉም ይዞ ይገኛል፡፡ ግልጹ መልካም ነገር ይዞ የመጣ ጉዳይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ትርጉም ከሥልጣን አወረደው፣ ከነበረበት ቦታ አስነሳው የሚል ትርጉም አለው፡፡ ስለሆነም በዚህ አግባብ ተማሪ ጣለለት የሚለው ትርጓሜ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት አጥፊዎች ተማሪዎች እንደሆኑ ይገልጻል፡፡ ቃል አቀባዮቹ ስለ1966 ዓ.ም. የፈነዳው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ሲናገሩ ወታደሩ ኋላ የመጣ ነው በማለት የተማሪዎቹን የፖሊቲካ እንቅስቃሴ ትልቅነት ይገልጻሉ፡፡ “ተማሪና ሴት ያነሳው ነገር አይበርድም፤ ጃንሆይን የጣለ ተማሪ ነው” ይላሉ፡፡ ከዚህም አንጻር ይመስላል <u>የተፈሪን[104] አልጋ ተማሪ ጣለለት</u> እየተባለ የተዜመው፡፡ በተጨማሪም በተደጋጋሚ እንደተገለጸው ንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣናቸውን ለአልጋ ወራሻቸውና ለቀጣዩ ትውልድ በክብርና በፈቃደኝነት አላስረክብም ቢሉም ጠንካራ ተከራካሪ ተማሪዎችን አምላክ ጣለባቸውና ወደቁ፤ ይህም ሁኔታውን “ከአልጋ ሲሉት ከአመድ” የሚል እንድምታ እንዳለው አስረጂዎቹ ይገልጻሉ፡፡[105]

---

[103]Bahru, 2008, pp, 253-265;Bahru Zewde፣.*Documenting the Ethiopian students Movement :an Exercise in Oral History(*2010), pp.1-141.

[104] አፄኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ከመሆናቸው በፊት ስማቸው ተፈሪ ስለነበረ ሕዝቡ እንደየ ሁኔታው ተፈሪ እያለ ይጠራቸው ነበር፡፡
[105]ሽመልስ፣ ዋኘው፣ በሬ፣ ሲሳይ፡፡

## 7.2. አካባቢያዊ ጭብጥ ያላቸው የቃል ግጥሞች

ከ1930ዎቹ ጀምሮ የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ ታማኝ እንደራሴዎች ባላባት ባልሆኑበት የሀገሪቱ ክፍል መሾም፣ የሹማምንቶች በቶሎ መቀያየር በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ እየሆነ በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው የፍትሕ መጓደልና አስተዳደራዊ በደል በማኅበረሰቡ ላይ እየተባባሰ የመጣበት ጊዜ ነበር፡፡ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ግጥሞችም ከንጉሡ ከሚከተሉት ከልማድ የወጣ ሥር ነቀል አስተዳደር ጋር በቀጥታ የሚገናኙ ናቸው፡፡

17) ስሙም አንዳርጌ ነው አንድ አድርጎ ገዛን፣
እንከን አልባው ጀግና የጠቅል ባለሟል፡፡

18) ሁሉ በሽተኛ ሁሉ ራሴን ባይ፤
ደህና ሰው ባገሩ ሊጠፋ ነው ወይ፤
አገሩ ጥጋብ ነው በሰሜን ሲሳይ፤
ውቤ ነህ !ውቤ ነህ !አንዳርጋቸው መሳይ[106]፡፡

በቁጥር 17 የተጠቀሰው ግጥም ከ1938-1944 ዓ.ም. የቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ገዥ ሆነው የተሾሙትን ቢትወደድ በኋላ ራስ አንዳርጋቸው መሳይ የንጉሡ የበኩር ልጅ የልዕልት ተናኘ ወርቅ ባለቤት የሆኑትን በማስመልከት ሕዝቡ በአስተዳደራቸው እንደተማረረ በመግለጽ ከአካባቢው እንዲቀየሩ የተናገረበት ነው፡፡ ይህን የሕዝብ ምሬትና ብሶት በአካባቢው ላይ የተሠሩ ምርምሮችም ያረጋግጣሉ፡፡[107] ለምሳሌ፤ ከመጀመሪያው ግጥም ሁለተኛው ስንኝ ላይ አስተዳደራዊ በደሎችን ሕዝቡ አምርሮ ይቃወም እንደነበር ይነገራል፡፡[108] ይህን ተግባር ለመበቀል ሕዝቡ ዕርስበርሱ አንዱ አንዱ ላይ እንዲዘምት ተደርጓል፡፡ ስሜን ወደ በጌምድር፣ በጌምድር ወደ ስሜን፣ እንዲሁም አንዱ አውራጃ ወደሌላው አውራጃ የዘመተበትም ጊዜ ነበር፡፡ ለዚህም ይመስላል "<u>አንድ አድርጎ</u>" ገዛን እየተባለ የተሸሚጠጠው፡፡

[106] አጋፋሪ አበበ አየለ

[107] Debash,2011, p,101; Solomon , 2006፣pp, 70-72)

[108] የንጉሠነገሥቱ መንግሥት በተለይ ከጠላት ወረራ በኋላ ለአርበኞችና ለጣሊያን አስተዳደር ላደሩት እኩል አንዳንዴም ባንዳ ለሚባሉት የተሻለ ቦታ በመሰጠቱ ቅሬታዎች በተለይ ከአርበኞች በኩል ሲሰሙ ይስተዋላል፡፡ አንዳንድ የአቤቱታ ማመልከቻዎች ችግሩን በውስጣቸው በመያዝ "የማንንም ውለታ የማይረሳው ንጉሠነገሥት ግርማዊነታቸው…" እያሉ የደብዳቤው ጽንሰሐሳብ ግን በደልንና ለሀገር ውለታን ያተረፉ ዜጎች እንደተበደሉ ማሳየታቸው አልቀረም፡፡ ለምሳሌ፤ አርበኛ ግራዝማች ሞትባኖር ተሰማና በእነ አቶ ደጀኔ መርዕድ፣ አቶ ሞላ ከልካይ በመካከል የነበረው ውርክብ ይህን የሚያሳየን ነው፡፡ ፋይል ቁጥር 76፣ ቤ/ጠ/ግ/ ደብዳቤ ቁጥር 12685/60/4670፣ 1952 ዓ.ም.፡፡

በዘመኑ ተጽፈው ለታሪክ ምርምር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ ያሉት መዛግብትም የወቅቱን የሕዝብ እሮሮ የሚያሰሙ ናቸው፡፡[109] ወደ ቁጥር 18 ግጥም ስንመጣ፣ ግለሰቡ በአስተዳደራዊ ችግር ከቋሚ ሥራው ተፈናቅሎ፣ ተበሳጭቶ ራስ ቢትወደድ አንዳርጋቸውን አስመልክቶ እንደተናገረው መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ፡፡ በገለጻውም የእነደጃዝማች ውቤ ስሜን ጠለምት ተወላጅነቱን ጠቅሶ በተደጋጋሚ ቢያመለክትም ሰሚ አላገኘም፡፡ ብሶቱንም "ውቤ ነህ ውቤ ነህ አንዳርጋቸው መሳይ" በማለት ከተወላጁ ደጃዝማች ውቤ ጋር ያመሳሰለውና ዝምድናውን የፈለገ በማስመሰል አሽሟጠባቸዋል፡፡ የቢተወደዱ ጊዜም ነገረሠሪ የበዛበት ስለመሆኑም ገልጧል፡፡ ከዚህም ባለፈ ልክ እንደሌሎች አምባገነን ገዥዎች ሁሉ ራስ ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሳይን ምክንያት በማድረግ ከቀድሞ ያልተለመደ ፍጹም በማእከላዊ ሥርዓት መመሥረቱ ነባሩን "ፌደራላዊ" ይዘት የነበረውን በአካባቢ ገዥነታቸው ተወዳጅ፣ ተሰሚና ተከባሪ የነበሩትን የጠቅላይ ግዛት ባላባቶች የራስ ገዝ ሥርዓትን ያኮሰሰ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ይህም የሆነው የማእከላዊ መንግሥት የሥልጣን ተጋሪና ተቀናቃኝ

---

[109] የንጉሠ ነገሥቱ ለም መሬቶችን አነፍንፈው ባለርስቱን እያፈናቀሉና ቀላድ እያስጣሉ ትርፍ መሬት ነው በማለት በቤተርስት ግምጃ ቤት ተወርሶ ወደ ግል ይዞታቸው የማስገባት ሥራ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል  በሚባል ደረጃ ይፈጽሙ ነበር (ዋጋው፣ 2012 ገጽ፣ 118-120)፡፡ በተመሳሳይ በጎንደር ከተማና በአካባቢዋ ባሉት ውሃ ገብ ለም መሬቶች፣ ለምሳሌ፤ አዘዞ አባሳሙኤል፣ ጎመንጌና ቸቸላ የአካባቢው ተወላጆች ፊታውራሪ ካሳ በለጠ፣ አደማሱ ተገኝ፣ አስፌ ደምሴ እንዲሁም ንጉሥ ወልደጊዮርጊስን ጨምሮ በነበረው የይዞታ መሬት ላይ የግርማዊ ቀዳማዊ ጃንሆይ ቤተሰቦች በቤተርስትነት ተተክለዋል፡፡ የኢጣሊያን መንግሥት ደረጃቸውን አስጠብቆ ያሰራቸው ቤቶችም ጭምር በንጉሡ ልጆችና የልጅ ልጆች ንብረትነት እንደተዘዋወሩ ቃል አቀባዮቼና ጥናቶች ያስረዳሉ (ስለሺ ደምለው፣ ወርቁ ገሰሰ፣ Girma, 2017, pp.12-13፣ ዋጋው፣ ገጽ፣194)፡፡ ልዕልት ተናኘወርቅ፣ ባላቸው ራስ አንዳርጋቸው መሳይ፣ ልዑል አስራተ ካሳ፣ እተጌ መነን አስፋው በኂላ አስፋወሰን ኃይለሥላሴ፣ መኮንን ኃይለሥላሴ፣ ራስ መንገሻ ስዩምና  በርካታ የጃንሆይን የልጅ ልጆች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ የጎላ ተጽዕኖ ከጣሊያን ጋር ሲከራከር ለነበረው ለጎንደር ሕዝብ መልካም የሚባል አልነበረም፡፡  የፊታውራሪ ካሳ በለጠ፣  አደማሱ ተገኘ፣ እንዲሁም የራስ ውብነህ ተሰማ ተቃውሞ ተጠቃሽ ነው፡፡ ሆኖም ተቃውሞው ሰሚ አልነበረውም፡፡ ጃንሆይ ከነጻነት በኂላ ጎንደርን ሲጎበኙ ለሕዝቡ የተናገሩት ንግግራቸው ጥያቄ የሚያስነሣ ነበር ( ወርቁ በዛብህ፣ ሲሳይ ቦጋለ)፡፡ ለምሳሌ፤ የስሜንና ቤጌምደር ሕዝብ ከጣሊያን ጋር ላደረገው የነጻነት ተጋድሎ አድንቀው፤ "ይህን የጣሊያን ሕንፃ ወደ አዲስ አበባ  የማይወሰድ ነገር ሆነብን" በማለት የተናገሩት ሕዝቡን ያስቆጣ ነበር፡፡ ንጉሡ ራስወዳድና ሚዛናዊነት ይጎላቸው ነበሩ የሚሉ ብዙ ናቸው፡፡ ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ዕውቁ ጥበበኛ ቀኛዝማች ምስጋናው

ዘርዝረን እናውጋው የሥላሴን ነገር፣

ዳግም "ዓለም ታዬ" ጠቅል መጥተህ ጎንደር፡፡

(በሁሉም፣ 2009 ዓ.ም፣ ገጽ፣ 87፣  ራዱ ብዙነህ)፡፡

እንዳይሆኑ በመሥጋት ነበር፡፡ በቀድሞ በአካባቢው ተወላጅ ባላባት የመግዛትና የመተዳደር ልምድን ለማፍረስ መሞከር ቀድሞ በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ በነገሥታቱና በጠቅላይ ግዛት ራሶችና ደጃዝማቾች መካከል የነበረውን የመከባበር ባህል የተጋፋ እንደነበር የዕድሜ ባለጸጎች ያብራራሉ፡፡[110] ልዑል ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ በመጽሐፋቸው ምንም እንኳን የቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛትን ጉዳይ እንደምሳሌ ባይወስዱትም በጎጃም ክፍለሀገር ስለነበረው ሁከት እንዴት ከነባሩ የአስተዳደር ባህል ጋር እንደሚገናኝ ያስረዳሉ፡፡[111] የራሳቸውን የአስተዳደር ጉዳይ መነቀልና መተከል የበዛበት ከሐረር ወደ ወሎ ከዚያም ጎጃም፣ በመጨረሻ ቤጌምድርና ስሜን እንደነበረ ያናገራሉ፡፡[112] በንጉሡ አጠራር "ካባ አጣፊዎች"[113] በማለት የሚጠሯቸውን ወደአዲስ አበባ በመውሰድ ደጅ እንዲጠኑና በሕግ መወሰኛ ምክርቤት እንዲቀመጡ በማድረግ፣ ታማኝነትን ብቻ ማእከል ያደረገ የቤተዘመድ ሹመት መቃወማቸውንም ያሳየናል፡፡ ስመጥሩው ራስ አሞራው ውብነህ ተሰማ እንደ ምሳሌ በቃል አስረጂዎቼ በተደጋጋሚ ይጠራሉ[114]፡፡

19) ጎንደር ከግንቡ ሥር ደጅ ጠኙ ሙቶ
በወገን ተፈታ ባላባት ቂስ አጥቶ፡፡[115]

ቁጥር 19 ግጥም የሚያተኩረው የሀገሬው ሰው በራሱ አባት አደር መሪዎች የመተዳደር የረጅም ጊዜ ልማዱ መገፈፉን፣ በዚህም ደስተኛ አለመሆኑን ነው፡፡ የበጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት በአልጋ ወራሽ አስፋወሰን ሳይቀር እስከ የጦር መሪዎች ድረስ ከጠላት ወረራ በኋላ የሀገሬው ተወላጅ ገዥዎች ያልተሳተፉበት ከማእከል በተሾሙ የአካባቢው ተወላጅ ባልሆኑ ሹመኞች ተመርቷል፡፡ ለምሳሌ፤ በ1934 ዓ.ም. ንጉሡ ልጃቸውን አስፋወሰንን በጠቅላይ ግዛቱ ሲሾሙ "… ለመልካም አስተዳደራችሁና ለልማታችሁ፣ ለኅብረታችሁ የምንደክምበትን ሥራ

---

[110]ዋኘው ዘዋለ፣ ወርቁ ገሠሠ፣ አበበ ማለደ፤ በክቡር አንዳርጋቸው መሳይ በጎፈቃድ ሥራ ማይችሉ ወገኖች ሳይቀር ለምሳሌ፤ ገብረሥላሴ ተሰማ የተሰኙ ግለሰብ ያለችሎታቸው በታማኝነታቸው ብቻ ተመዝነው በወገራ አውራጃ ክንፋዝ ምክትል ወረዳ ጸሐፊነት በ1938 ዓ.ም. መሾማቸው ውዝግብና የሥራ መበደልን አስነስቶ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ፍትሓዊና ልማዳዊ አስተዳደራችን ይከበርልን በማለታቸው ከመንግሥት ጋር ጦርነት ከገጠሙት የጠቅላይ ግዛቱ አካባቢዎች ከምከም ቃሮዳ አንዱ ነበር፡፡ በዚህ ጦርነት ከመንግሥት በኩል የተሳተፉት የሸዋ ሰው ፊትለወርቅ ዘለቀ የተባሉ ስለውለታቸው በገብረሥላሴ ተሰማ ቦታ ተሹመዋል፡፡ ሁለቱም ግለሰቦች ግን ባላባትነት የሌላቸው፣ ከሌላ የሀገሪቱ ክፍል የመጡ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፋይል ቁጥር 3553/60 ቤ/ጠ/ ግ/፣ ቀን ሚያዚያ 11/1941፡፡

[111]እምሩ ፣ካየሁትና… ገጽ፣192

[112] ዝኒከማሁ፣ 172

[113] አለባበሳቸውን አሳምረው ሕዝብን የሚበድሉ ለመንግሥትም ሥጋት የሆኑ ባላባቶች፡፡

[114] (አጋፋሪ) አበበ ማለደ እና ሽመልስ ደምለው ፡፡

[115] መረጃ ሰጪ፡- በሬ ፉሌ

ለማስፈጸም… ለስመጥሩው የቤጌምድር ሕዝባችን የሚያስተዳድራችሁ ገዥ የተወደደ ልጃችንንና አልጋወራሻችንን ልዑል አዝማች አስፋወሰንን ሰጥተናችኋልና የሱን ቃል ሰምታችሁ አክብራችሁ እደሩ።"[116] በማለት ደብዳቤ ጽፈው ነበር። ብዙ የመምራት ዐቅምና ለሀገር ክብር የተጋደሉ ጀግኖች ያሉበት ሆኖ ሳለ ሥልጣኑ ተወስዶበት በሌሎች ይሁንታ መተዳደሩ ፍትሕ፣ ሰላምና መርጋጋት እንዳይኖር እንዳደረገው ይናገራል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የሕዝቡን ብሶት ለመግለጽ የሚከተለውን ጥቅስ መመልከቱ ግንዛቤን ይጨምራል። "የሀገሩ ሕዝብ ... ከውጭ ከሚመጣው ጠላት ጋር እየተዋጋ በውስጥ ደግሞ አንድነቱን የሚያፈራርሱትን ግብዞች እየደመሰሰ ያኖረውን ሀገር የሸዋ ሚኒስትሮችና የሸዋ ሰው እየቆራረጠ በገንዘብ ሲሸጠው ዝም ብሎ ለማየት አይቻለውም…"[117] ከዚሁ የአስተዳደር ፍትሓዊነት ጥያቄ ጋር ተያይዞ ሕዝቡ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የለውጥ ፍላጎቱን ሲገልጽ ይስተዋላል። ለምሳሌ፤ አንድ የደብረታቦር አውራጃ ባላባት አባተ አበጋዝ የተሰኙ ጉዳያቸውን እስከ ንጉሠነገሥት ችሎት፣ ሀገር ግዛት ሚኒስቴር፣ እንዲሁም ለቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ገዥ ሳይቀር ከአያት ቅድመ አያት ጀምሮ በቅንነት አገልጋይ መሆናቸውን በመጥቀስ የተወሰደባቸውን የአባታቸውን ሥራ ለማግኜት ለረጅም ጊዜ ደጅ ቢጠኑም፣ "አስተዋይና አቅራቢ ወገን" በማጣታቸው ለ20 ዓመት አዲስ አባባ ጎንደር ሲመላለሱ ኖረዋል። ማመልከቻው ላይ ግለሰቡ".... ሃብታም፣ ዘመድና ባዕድን በማይለየው አምላክ በሰማይ በኩል አስጎዳለሁ…" የሚል ሐሳብ ይነበባል። እኚህ ግለሰብ በጻፉት ማመልከቻ እንደሚታየው ደጅ ጥናት መደበኛ ሥራቸው በሆኑን ጭምር ያስረዳናል። ጉዳያቸው እስከ መጨረሻው መፍትሔም አልነበረውም፤ ምናልባት በአብዮቱ የተቋጨ ይመስላል።[118]

20) እጅ የሚያስነሳው ሰው እርሱ እጅ እየነሳ

አባ መብረቅ ዘውዱ ሳይገዛ ሄደሳ።*[119]*

የቁጥር 20 ግጥም የሚያወሳን ባንድ ወቅት የአባ ይርጋ[120] አያሌው ብሩ ልጅ እና የኮሪያ ዘማች የነበሩት ሻለቃ ዘውዱ ፓርላማ ለመግባት በትውልድ ሀገራቸው ወገራ ስሜን እጩ የምርጫ ተወዳዳሪ ሆነው ቀርበው ነበር። ሆኖም ግን ሕዝቡን በማኅበራዊም ይሁን ፖለቲካዊ ብሶቶቹ ዙሪያ "ጠይቀውት" ስለማያውቁና በተድላ አዲስ አበባ የሚኖሩ በመሆናቸው

[116] Girma, p.8

[117]Solomon Adis Getahum, *A History of the City of Gondar*. (Trenton: African world Press, 2006), P.23.

[118] ፋይል ቁጥር 81/ቤ/ጠ/ግ/ ደብዳቤ ቁጥር 3230152፣ ሰኔ 1955 ዓ.ም።

[119] ስለሺ ደምለው

[120] የደጃዝማች አያሌው ብሩ የአረስ ስም

አናውቅህም ብሎ ሳይመርጣቸው ቀረ፡፡ "እጅ የሚያስነሳው ሰው እርሱ እጅ እየነሳ" በባላባትነቱ የተነሣ ሰዎች ለእርሱ መጎናበስ ቢኖርባቸውም እንዳላደረጉት ያሳያል፡፡ ይህም በግለሰቡ፣ በሥርዓቱም ያልተደሰቱ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ሕዝቡ ተወዳዳሪው ለፓርላማ ባለመመረጣቸው የተጸጸተ በማስመሰል ደስታውን እንደገለጸ እንረዳለን፡፡ ከሻለቃ ዘውዱም በኩል "ተቆርቋሪ" በመምሰል አንዲት የጎንደር ቤተመንግሥት አዝማሪ የሚከተለውን ገጥማለች፤

21) አገሬ ነው ብዬ ሳወራ ሳወራ
ይመርጠኛል ብዬ ስኮራ ስኮራ
አላውቅህም አለኝ ሰው አጥፊው ወገራ፡፡[121]

በቁጥር 21 ግጥም እንደተገለጸው፣ ባለጉዳዩ ሕዝቡ እንደተቀየመ ተረድቶ እንደሄደ ያስረዳናል፡፡ በሦስተኛው ስንኝ ሰው አጥፊው የሚለው ሐረግ ሁለት ትርጉም ያሳየናል፡፡ አንደኛው የሻለቃ ዘውዱን በአካባቢው ሰው "መረሳትን" ሲያሳየን፣ ሁለተኛውና ዋናው ግን ሕዝቡ ብልኀና ማገናዘብ የሚችል፣ ሳልሆነለት የማይሆን፣ ከወደደ የሚወድ፣ እንዲሁም ከጠላ የሚጠላ መሆኑን መስክሮ አድንቆና ተገርሞ እንደሄደ ተንታኞቹ አስረድተውኛል፡፡

ከጠላት ወረራ በኋላ የንጉሡን አስተዳደር በመቃወም በገጠርም ሆነ በከተማ ለሚደረጉ ንቅናቄዎች ከመንግሥት አካላት የሚሰጠው ምላሽ በጎ አልነበረም፡፡ ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢም ተመሳሳይ ምላሾች ነበሩ፡፡ ሕዝቡ ቅሬታ ሲያቀርብ ምላሹን በሰላም ከመፍታት ይልቅ ወደ ኀይል ያመዘነ ነበር፡፡ ለምሳሌ፤

22) እሰይ የምስራች በሬ ሳር ከበላ
እምሩ በገመድ አርአያ በዱላ፣
ሌቦ ተፈጸመች ከእንግዲህ በኋላ፡፡
23) አልሞላለት ቢለው የቤቱ ጉዳይ፣
ጀግናው ገበያ ወጣ ካንገቱ በላይ[122]፡፡

በቁጥር 22 የቀረበው ግጥም የራስ እምሩ ኃይለሥላሴን እና የደጃዝማች አርኣያ ገብረመድኅንን አስተዳደር ይመለከታል፡፡ በነዚህ ባለስልጣናት

[121] ዝኒከማሁ
[122] ስለሺ ደምለው ፡፡

አስተዳደር ጊዜ ሕዝቡ ለምን ዐመጸ? ምክንያቱስ ምን ነበር? የሚል ጥያቄ ማንሣት ክልክል ነበር ይላሉ-ቃል አቀባይዎቼ። በፖለቲካ ልዩነት ምክንያት በረሃ የወጣው ጃጉሳ /ሽፍታ/ ጨለማ ለብሶ "ሌባ አይደለሁም፤ "የከፋኝ ነኝ" ብሎ ነዋሪዎችን ምግብ ይለምናል። ነዋሪዎችም ቤት ያፈራውን በድብቅ ይዘረጉለት እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ሆኖም ግን ከመንግሥት ባለሚሎች በኩል ሌባ ተብለው ይፈረጁ ነበር፤ ወታደርም ሕዝቡ ላይ ይዘምት ነበር። ለምሳሌ፤ ከ1937-1940 ዓ.ም. ለነበረው የሕዝብ ዐመጽ ለአልጋ ወራሹ የተጻፈው ደብዳቤ እንደሚያመለክተው ከሕዝቡ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ሳይሆን ትኩረቱ ዐመጹን ከማስቆም ላይ ነበር፤ "መጥፎ ሐሳብ ያላቸውን ወስላቶች መለቃቀም ያሻል" በማለት መረጋጋትንና ሰላምን ለማምጣት ያለው አማራጭ ተብሎ የተወሰደው ኀይል ብቻ እንደነበር እንረዳለን።[123] ከላይ የተጠቀሱት ገዥዎችም ይህንኑ ተግባር ሲተገብሩና ሕዝቡ ጭንቀት ውስጥ እንዲገባ ምክንያት እንደነበሩ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሕዝቡ ብሶቱን ሲገልጽና መፍትሔውንም ሲያስቀምጥ ለአብነት ያህል፣ የራስ እምሩን አስተዳደር መጥቀሱ መልካም ሳይሆን አይቀርም። "በሀገሩ ላይ የጦር ኀይል ሰፍሮ ከሚያስፈራራው ይልቅ አብልጦ የሚፈራውና የሀገሩም ጸጥታ የሚከበረው "ደንቆሮም" ቢሆን እንኳ ስሙ በታወቀ "ሀገረ ገዥ" በሀገሩ ላይ ሲቀመጥ ብቻ ነው። ስለዚህ ክቡር ራስ እምሩ … በፍጥነት እንዲሄዱ ቢገደዱ የተሻለ ይሆናል።" በማለት ብሶቱን[124] ግጥሞቹ "የኔ ቢጤ ተራ ሰው" ሲያያቸው ሰላምና መረጋጋት ያመጡ ገዥዎች ተመስለው፣ በመላው ሕዝብ የሚወደዱ ተደርገው ነው የቀረቡት። "<u>በሬ ሣር ከበላ</u>" ሲል በሬ በሌባ ሳይወሰድ እንደልቡ ውሎ ከገባ የሚል መልዕክት ያለው ሳይሆን አይቀርም። በተጨማሪም በቁጥር 23 የተመለከተው ስንኝ እንደሚነግረን ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ በስቅላት እንዲሞቱና ገበያ የዋለውና ያለፈ ያገደመው እንዲያያቸው የተደረጉት፣ ሰዎች እንደቃል አቀባዮቼ ከሆነ አስተዳደሩን የተቃወሙ እንጂ የሌብነት ጣጣ ያለባቸው አልነበሩም።[125] ይህን ሐሳብ ለማጠናከር ይመስላል አዝማሪዋ <u>"አልሞላለት ቢለው የቤቱ ጉዳይ</u>"[126] እያለች የሀገር ችግር እፈታ ብሎ ለስቅላት በቃ በማለት የተናገረችው። ይህን ሐሳብ ለማጠናከር በሚመስል ሌላ ስንኝ፣

---

[123]Debash, 2011

[124]Solomon, Gondar...pp.70-71

[125]አቶ በያን ገበያው ዕድሜ 55፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቦታ ጪሂት፤ 3-8 /02/2005 ዓ.ም.

[126] የከምከም ሽምብራ የመቀጣዋ አተር
አልቤን እምቢ ብሏል አንተው ተጠናከር።
የአካባበው ሕዝብ ክፉኛ በጦር በመጎዳቱ፣ የመንግሥትን ግፍ ከግምት በማስገባት የሕዝቡን ደም አተርና ሽምብራው ሳይቀር ለበላው መርዝ እንዲሆንበት በመመኘት የቋጠሩት ግጥም ነው። ብዙ ወታደርም በሽምብራና አተር እሸት እንደሞተ ይነገራል (Debash Yimam, 2011, p. 95-105).

24) ገበሬ ዓመት አርሶ እግዚአብሔርን ያማል
ያደለው ሰውማ ወራርሶ ይበላል።

25) ነገሩ በውበት የሚያልቅ መስሎኝ፣
እሄዳለሁ ጎንደር ከበየነልኝ[127]።

ግጥም 24 የሚያስገነዝበን የኢትዮጵያን ገበሬ የሕይወት ውጣ ውረድን ይተነትናል። ገበሬው ሕይወት ውስጥ ፈጣሪ አምላክ ትልቅ ቦታ አለው። “ገበሬ ሞኙ መጀን” እንዲሉ ገበሬ አምላኩን በማመን እህሉን አውጥቶ ከአፈር ቀላቅሎ ምርት ይጠብቃል። ዝናቡን የሚሰጠው ፈጣሪው ነው፤ ምርቱንም እንዲሁ። ያም ሆኖ ከአምላኩ ጋር የሚሟገትባቸው ጉዳዮችም አሉት፤ በተለይ አዝመራ ሲከዳውና ምርቱን ለኔ ባዩ ሲበዛበት። ምርቱን በዛም አነሰም የሚያገኘው በዓመት አንድ ጊዜ ከስንት አቤቱታና ጭንቀት በኋላ ነው። አንበጣ ሊበላበት ይችላል፤ የዝናብ እጥረት ሊከሰት ይችላል። ሌላም ከእርሱ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ሁሉ ሲያሳስበው ይቆያል። የመጀመሪያው ስንኝ የሚነግረን ይህን ነው። “የኑሮ እኩሌታ” እንዲሉ ሁለተኛው ስንኝ ላይ “ያደለው ሰውማ ወራርሶ ይበላል” ይላል። ይህ የሚነግረን ነገር አንዳንዶች መሬት በስፋት ያላቸው በሎሌ አሳርሰው ብዙም ሳይለፉ የተድላ ኑሮ ሲኖሩ ይታያሉ። በአጭር ጊዜ ምርት ሊያገኝ ይችላል የሚልም ይመስላል። ሌላውና በዋናነት የተቀመጠው ጉዳይ ወራርሶ እሚለው ውስጠ ታዋቂ ትርጉም ነው። ይህም በመተያያ፣ በስጦታ፣ በጉቦ፣ በገጸበረከት እየሰበሰበ በሰው ትከሻ ይኖራል የሚል እሳቤን የሚያስረዳ ነው። ተግባሩ ጥሩ እንዳልሆነ በምጸት “ያደለው ሰውማ” እያለ ያሽሟጥጣል። ከፍተኛ ባለሥልጣናት እንኳን ሳይቀሩ የሕዝብ ሀብት እንደሚመዘብሩ በሚከተለው መልኩ መታዘብ ይቻላል። ለምሳሌ፤ ከ1934-1936 ዓ.ም.፣ እንዲሁም ከ1944- 1948 ዓ.ም. የበጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ገዥ የነበሩት ልዑል ደጃዝማች አስራተ ካሳ በ1935 ዓ.ም. በግዛቱ ለሚገኙ መንገዶች ማደሻ የሚሆን 10,000 ጠገራ ብር ከማእከል ተልኮላቸው ገንዘቡን ለግል

[127]ስለሺ ደምለው፣ Solomon, Gondar.. , p.115.

ጎንደሮች ሲቀኙ እየቆጠሩ ነው
አዘራረፍ ማወቅ እንደተገኝ ነው።

ተገኝ የተባለ ዳኛ ሕዝብን ጉቦ አምጡ እያለ ሲያስቸግር ኖሮ በቅኔ ንጉሡ ባሉበት ግብር ላይ አዝማሪ እንዲቀኝበት ተፈልጎ እንዲመጣና ከሥራው እንዲሰናበት እንደተደረገ ይነገራል። በሁሉም 2009 ዓ.ም. ግጥሙን ከቀኛዝማች ምስጋናው አዱኛ ጋር በማያያዝ የኢፍትሓዊ ጉዳዩን አብራርታ ጽፋለች።

[127] ዝኒከማሁ።

ጉዳያቸው እንደአዋሉት መረጃዎች ያስረዳሉ።[128] በአንዳንድ የጠቅላይ ግዛቱ መሪዎችም ለምሳሌ፤ ኮሎኔል ታምራት ይገዙ (1957-1966) እንደሌሎች ገዥዎች ሁሉ ሕዝቡ በጉቦ፣ በኢፍትሓዊ አሠራር የተከፋበት ዘመን ነበር።[129] የገዥውንም ዘመን "በታምራት እንኳን ምሳ የለም እራት"[130] እያለ ከእጅ ወደ አፍ ኑሮው ላይ ሌላ ጫና እንደነበረበት ችግሩንና ብሶቱን በተናጋሪዎቹ በኩል እንደተናገረ መረጃዎች ይጠቁማሉ።[131]

በግጥም 25 እንደተመለከተው፣ አንድ የአውራጃ ፍርድ ቤት ዳኛ በስም አለቃ ውበት የሚባሉ ለአንድ ነዋሪ ፍርድ አዛብተው ፈርደውበት የጠበቀው ነገር ባለመሆኑና ጉዳዩ ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ለይግባኝ የማያስኬደው አስመስሎ ዳኛው አለቃ ውበት ኅበዝ፣ ብልኅ፣ ነገር ዐዋቂና ፍትሓዊ ናቸውና ጉዳዬን በቶሎ ሳልንገላታ ይፈቱልኛል በማለት አሽሟጠዋል። ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጎንደር ብሄድም በየነ የሚባል ሰው አለ፤ እርሱን ደግሞ ሂጄ ደጅ ልጥና፤ ምናልባት ቢፈርድልኝ (ቢበይንልኝ) የሚል የተወሳሰበ የዳኝነት ሥርዓት እንደነበር ይጠቁመናል። ባለጉዳዩም የዳኞቹን ስም በመጥቀስ የተቀኙና ያመሰገኑ በማስመሰል በዘመናዊ ፍርድ ቤት የነበረውን ችግር አሳይተውናል። ከዚሁ ኢፍትሓዊነት ጋር በተያያዘ አለቃ ይማነብርሃን የተሰኙ የጎንደር ነዋሪ መሬታቸው በጭቃ ዳኛ ተይዞባቸው ወደጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሊሉ ፈለጉና ዳኞቹን አግኝተው ብርንዶ ሥጋ አብልተውና ጠጅ አጠጥተው ወደቤታቸው ይመለሳሉ። በማግስቱ ወደ ፍርድ ቤቱ ሲሄዱ መሬቱ ለባላንጣቸው ተወሰነ። በዚህም ተገርመው ባደባባይ "የሥጋ አምላክ" ይይላችሁ* ብለው ሄዱ ይባላል።[132] እዚህ ላይ ሰውየው ስላልተፈረደላቸው ከዳኞቹ ጋር የሥጋ ዝምድና ያላቸው

---

[128]ስለሺ ደምለው፣ Solomon, p.115 ይመልከቱ።

[129] ገብሩ ካሳ፣ "የደብዳቤዎች አምድ"፣ *ትዕይንተ ጎንደር መጽሔት* 1966 ዓ.ም.፣ ገጽ፣2-3፤ ላይ በስፋት የተጻፉት ግጥሞች የዘመኑን ኢፍትሓዊነት የሚገልጹ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ፤

"በዘረፋ ገንዘብ ቤት ውስጥ ተሞሽሮ፣
እስከ መቼ ድረስ በደል ይስማ ጆሮ…። እያለ ይቀጥላል።

[130] ምንም እንኳን ዘርፈብዙ አስተዳደራዊ ችግሮች ቢስተዋሉም አንዳንዴ ለማኅበራዊ ፍትሕ ጥንቃቄ ሲደረግም ይስተዋላል። ለምሳሌ፤ ግራዝማች ቀለተ ገብረመስቀል የተባሉ ባለሙያ በጭልጋ አውራጃ በደንገልበር ክሊኒክ ሠራተኛ፣ በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ደብራዋ ከሚባለው ከተማ ቦታ ክርክር ስለነበረባቸው በየጊዜው ይመላለሱ ስለነበር በአስቸኳይ ጉዳያቸው እንዲፈጸምላቸው የጭልጋ አውራጃ ገዥ፣ ፊታውራሪ ፈረደ ጥሩነህ በቁጥር 1413/29 በቀን ታኅሳስ 7/1961 ዓ.ም. የተጻፈው ደብዳቤ በክፍለሀገሩ እንደራሴ ፊታወራሪ በቀለ ዘለለው ታምኖበት ወደሚመለከተው ተላልፎ መፍትሔ እንዳጣ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ፋይል ቁጥር 79/ ቤ/ጠ/ግ/ ደብዳቤ ቁጥር 6/አገ42.28/42፣ ታኅሳስ 9/ 1961 ዓ.ም.።

[131] Debash,p.118; ስለሺ ደምለው፣አበበ ማለደ።

[132]ዝኒከማሁ።

በማስመሰል የዝምድና አምላክ ይፍረድባችሁ በሚል መልኩ ዳኞቹን በሽሙጥ ነካ አድርገዋቸዋል፡፡ የዳኝነት ሥራም በዝምድና እንደሚሠራ የሚያሳይ ነው፡፡[133] በሌላ ውስጠ ታዋቂ ሥጋ አብልቼ፤ ጠጅ አጠጥቼ እንዴት መሬቴን ለባላንጣዬ ትሰጣላችሁ የሚል ትርጉም አለው፡፡ በዚህም የዘመኑን የዳኝነት ሥርዓት በሰላ ቋንቋ አሳይተውናል፡፡

## 8. መደምደሚያ

ጥናቱ በግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ሥርዓት "የተራውን" የማኅበረሰብ ክፍል ፖሊቲካዊ ንቃተኅሊና ከሞላ ጎደል ለማሳየት ሞክሯል፡፡ የአስተዳደር በደልን፣ ለንጉሡ ነገሥቱ ሥርዓት ያለውን ዕይታ፣ የፍርድ መጓደልንና የኢኮኖሚ ውድቀትን በማንሣት ሐሳቡን በቃል ግጥሞች ያሰማ እንደነበር መረዳት ይቻላል፡፡ ጥልቀት ያለው የፖለቲካ ባህል በማኅበረሰቡ ውስጥ እንደነበረም ለመታዘብ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

ከ1933-1966 ዓ.ም. ባለው ጊዜ የቃል ግጥሞቹ የንጉሠ ነገሥቱን መልካም ሥራዎች፣ እንዲሁም ቀስበቀስ እያደገ የመጣውን ነባር ባላባታዊ ልማድን የማያከብረው ፍጹም ማእከላዊ አስተዳደራቸውንና አካባቢያዊ ግብረመልሱ ምን ይመስል እንደነበር ለመተንተን ሞክሯል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሕዝቡን ወቅታዊ ጥያቄዎችና ብሶቶች ግጥሞቹ ጠቁመዋል፡፡ ሕዝቡ ያነሣቸው ጥያቄዎች በወቅቱ የሀገሪቱ ሕዝብ ገባሩና ምንዝሩ፣ ጭሰኛውና ተጠመኙ፣ ተማሪውና ምሁሩ፣ እንዲሁም ተራማጅ ባለሥልጣናት ከሚያነሷቸው የአስተዳደር፣ የፍርድ፣ የመሬት፣ ግብርና መሰል ጥያቄዎች ጋር የሚመሳሰሉ መሆናቸውን የቃል ግጥሞቹ ይዘት አስረጂዎች ናቸው፡፡ እንደዚሁም ኅብረተሰቡ ሀገርንና ፖሊቲካን እንዴት ያየዋል? ብሶቱንና ምሬቱን እንዴት ይገልጻል? የሚሉትና ተዛማጅነት ያላቸውን ጉዳዩች ከቃል ግጥሞቹ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

---

[133] ባላምባራስ መንግሥቱ ታዬ የተባሉ ታሪክ ዐዋቂ ለሻለቃ መላኩ ተፈራ የጎንደር ክፍለ ሀገር ዋና አስተዳዳሪ ለነበሩት ነሐሴ 10 ቀን 1970 ዓ.ም. በጻፉት ማስታዎሻ "ባለታሪክ እንዲሆኑ ለማሳሰብ ነው" በተሰኘው አርዕስት ወደኋላ በመመለስ ጠቅላይ ግዛቱን ያስተዳደሩትን ወገኖች ዘርዝረው፣ ባለፈው 80 ዓመት እስከ አብዮቱ 1966 ድረስ በትንሹ 19 ትልልቅ መሳፍንት እየተፈራረቁ ሰፊውን ሀገር ቤጌምድርንና ስሜንን እንደገዙ መስክረዋል፡፡ ዛሬ ለተተኪው ትውልድ ትምህርትና ምሳሌ የሚሆን ቅርስ ትተው እንዳልሄዱ ገልጸው፣ ሆኖም ከድክመቶቻቸው መማር እንደሚያስፈልግ ለአስተዳዳሪው አሳስበዋል፡፡ ፋይል ቁጥር 97/ ጎ/ክ/ 20123556/70/ 10/12/1970 ዓ.ም፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች

መስፍን ኃይሉ፡፡2002፡፡*አደራ! ኢትዮጵያን በደማቸው ያስጠበቁ ጀግኖችና የጀግንነት ግጥሞች*፡፡ አዲስ አበባ፤ ማንኩሳ አሳታሚ፡፡

መርሰዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ፡፡2009፡፡ *ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ 1922- 1927*፡፡ አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ልዑል ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ፡፡2009፡፡*ካየሁትና ከማስታውሰው*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ዮፍትሔ ንጉሤ (ቀኝጌታ)፡፡2007፡፡*አጭር የሕይህወትና የጽሐፍ ታሪክ 1887-1939*፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ተክለ ሐዋሪያት ተክለማሪያም፡፡2007፡፡*ኦቶባዮግራፊ (የሕይወቴ ታሪክ)*፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

በሁሉም አለበል፡፡2009፡፡*ታሪክን በቅኔ፤ ቀኛዥማች ምስጋናው አዱኛ 1883-1964*፡፡ አዲስ አበባ፤ አልፋ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ማኅተመሥላሴ ወልደ መስቀል (ብላቴን ጌታ)፡፡1961፡፡ *ቼ በለው!* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አክሊሉ ሀብቴ፡፡2017፡፡*የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ታሪክ የከፍተኛ ትምህርት በቋቋምና መስፋፋት ጉዞ በኢትዮጵያ*፡፡ ታይዋን፤ ፕሪንሪነገ ፕረስ፡፡

ይኩኖአምላክ ገብረሥላሴ (አለቃ)፡፡1966፡፡ "የቀድሞ ቅኔዎች ከነትርጓሜአቸው"፡፡ *የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መጽሔት*፣ Vol. IV, No.1.

አርኖ ሚሸል ዳባዲ ፡፡ ተረጓሚ ገነት አየለ፡፡ 2009፡፡ *በኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች ቆይታዬ*፡፡

አይናለም አሸብር፡፡2007፡፡*ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ሥራዎች*፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ዋጋው ቦጋለ፣ *ቤተ-ርስት ሥልጣን መዋዕለ-ንዋይ እናበጎአድራጎትበቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሕይወት (1933-1967)*፣ አሳታሚየለውም፣2012 ዓ.ም)፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡2002፡፡*የስነ ጽሑፍ መሰረታዊያን*፡፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጥሩነህ ዜና፡፡2000፡፡“የኢትዮጵያ ዘመናዊ ድፕሎማሲ አጀማመርና ሂደት (ከነጻነት እስከ አብዮት)”፡፡ *የማህበራዊ ጥናት መድረክ*፡ ከድህነት ወደ ልማት፡- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ ሁለተኛ እትም ፣ቁጠር ስድስት፡፡ አሳታሚ ማኅበራዊ ጥናት መድረክ፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡1991፡፡*የስነቃል መመሪያ*:: አዲስ አበባ፤ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም::

________፡፡1994፡፡*ሰሚ ያጡ ድምፆች*፡፡ አዲስ አበባ፤ ብራና ማተሚያ ድርጅት::

________፡፡2004፡፡“ቁዘማ፤ (ፎክሎር)” *ባህልና ልማት በኢትዮጵያ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች አርታኢ ሽፈራው በቀለ*፤አዲስ አበባ፤ አሳታሚ ፎረም ፎር ሶሻል ስቴዲስ፡፡

*ገሪማ ታፈረ*፡፡1949፡፡*ጎንደሬ መጋሻው*፡፡ አዲስ አባባ፤ተስፋገብረሥላሤ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጌቴ ገላዬ፡፡2000፡፡"ከ1983 የመንግሥት ለውጥ በኋላ የምስራቅ ጎጃም ገበሬዎች ፖለቲካዊ ግጥሞች"፣ *Proceeding of the XIV International Conference of Ethiopian Studies*, Volume,3.

Abrams, M.H. 1981. *Glossary of literary terms*. New York: Cornell University.

Andrew J. Carlson, Dennis G. Carlson(1998).Vilegization in agrowing Ethiopian Town:Kossoge ,1963-1998. North East African Studies, Volume 5, Number 2, p,121, Michigan State University Press.

Ayichew Adisu. 2001. “Geledeba and Aykel the twin Towns of Chilga 1270-2000.” Unpublished B.A Thesis, AAU.

Bahru Zewde (ed.). 2010. *Documenting the Ethiopian students Movement: an Exercise in Oral istory*. Addis Ababa: Forum for Social Studies.

___________. 2001. *A History of Modern Ethiopia 1855-1991.* Second edition, Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

___________. 2002. *Pioneers of change in Ethiopia: The Reformist Intellectuals of the early Twentieth century.* OUP.

___________.2008.*Society state and History selected Essays*. Addis Ababa University press.

Bairu Tafla .1987. (translated.) Asma Giyorgis and his work “History of [Oromo] and the kingdom of sawä”. Stutgart: Franz Stiener.

Crummey. D. 2006. “Literacy in Oral Society: The case of Ethiopian Land records”. Journal of African Cultural Studies, 18(1): 9-22.

Debash Yimam. 2011.“The History of Wagara Warada to 1974”. Unpublished M.A Thesis in History A.A.U.

Desalegn Rahmato. 2009. *The Peasant and the State Studies in Agrarian Change in Ethiopia 1950-2005*. Addis Ababa University Press.

Ebrahim Damtew**.** 2018.**"**History through oral poetry: Peasant Responses to Land Reform and Land Redistribution in Gondar

province, 1975-1982", *Northeast African Studies*, Vl.18,Nos.1-2.

_________ . 2017."The shifting status of the Gondar Azmari in Revolutionary Ethiopia: from out cast to popular stars", *Ethiopian Renaissance Journal of Social Science and Humanities.* 4, 1.

________. 2013. "Observing Ethiopian Minstrels: an Indigenous Musicians and Singers (*Azmari)* in North Gondar zone" *The Asian Man - An International Journal.* Vol 7, India.

Fasil Kiros. 1993.The Subsistence Crisis in Africa: The Case of Ethiopia. Organization for Social Science Research in East Africa Press.

Feinberg, L. 1967. Introduction to satire Iowa: Iowa State University press.

Fekade Azeze. 1998.*Unheard voices: drought famine and God in Ethiopian oral poetry.* Addis Ababa University Press.

Fekade Azeze. 2006. *Ethiopia the Challenge of Democracy from below. Forum for Social studies,* in Bahru Zewde and Pausewang,Siegfried (ed.)"Oral Literature Depicting the man, His Regime officials and proclamations". Addis Ababa. *Forum for Social Studies Press.*

Gebru Tareke. 1996. *Peasant Revolts in the Twentieth Century*. The Red Sea Press.

Getie Gelaye. 1999. "Peasant Poetics and State Discourse in Ethiopia: Amharic Oral Poetry as a Response to the 1996–1997 Land Redistribution Policy," *Northeast African Studies* 6, nos.1–2, New Series.

Girma Tayachew. 1917. "The Administration of Italian buildings and holdings in Gondar Town 1941-1974" ,*EJSS* ,Vo.3.

Gordon, I. 2008. "Satire" *The literary Encyclopedia*: The literary Dictionary Company.

Harris, R. 2008. *The purpose and method of satire*: www.virtual salt. Com satire Atm.

Ishikawa, H. 2002. "Change in the Military System during the Gondar Period 1632-1767: the influence on the decline of the Solomonic dynasty" *In: Annalesd' Ethiopie*. Vol. 18.

Marcus, H. 2000. The Ango- Ethiopia treaty of 3January 1942: Did Ethiopia became a British Protectorate? *Proceeeding of the XIV*[th] *International Conference of Ethiopian Studies*, Baye

Yimam etal. (ed. ) Vol.I, Addis Ababa Uiversity.

Markakis, J. & Nega Ayele. 1977. *Class and Revolution in Ethiopia*. Review of African Political Economy, Taylor& Francis.

Merid W. Aregay. 1997. "Military elites in Medieval Ethiopia", *Journal of Ethiopian Studies*, Vol.30, No.1.

Misganaw Andualem. 2011. "Change and continuity in the lives of BurbuaxAzmaris in Gondar Zuria woreda." Unpublished MA Thesis, Department of Social Anthropology; A.A.U.

Ruth Finnegan. 1977. *Oral poetry*. London: Cambridge University press.

Sentayehu Genet. 2008. "Political and Social Satire in Bewketu Siyoum's Enqilf ena Edimie and Berari Kiteloch''. Unpublished M.A Thesis, Bepartment of Foreign language and Literature; A.A.U.

Solomon Adis Getahun. 2006. *Ahistory of the City of Gondar.* Trenton: African world press.

Teclehaimanot G/sillassie. 1986. "A brief survey for the study of the Azmari in Addis Ababa" *In the proceeding of the international symposium for the centenary of Addis Ababa,* edited Ahmed Zekaria, Bahru Zewde and Taddese Beyene A.A.U, IES.

Teshale Tibebu. 1995. *The Making of Modern Ethiopia 1896-1974*. Red Sea Press.

Tsehai Berhane-Sellassie. 2018. *Ethiopian Warrior hood: Defence, Land and Society 1800-1941*.Suffolk, UK: James Cureency.